# የእምነት መሰረቶች ትንታኔ

## شرح أصول الإيمان

17

باللغة الأمهرية

المسابقة الثقافية
الرمضانية السابعة عشر
للجاليات ١٤٣٦هـ

# የእምነት መሠረቶች ትንታኔ

ሸይኽ ሙሐመድ ብን ሷሊሕ ብን
አል-ዑሰይሚን

ተርጓሚ – ሙሐመድ ጀማል ሙክታር

አሳታሚ
እስላማዊ ዳዕዋና ዕውቀት ማህበር
አዲስ አበባ ህዳር 1985

መብቱ በህግ የተከበረ ነው
(All Rights Reserved

بسم الله الرحمن الرحيم

## بسم الله الرحمن الرحيم

ምሥጋና ለአላህ ይገባ። እናመሰግነዋለን። ረድኤት ከርሱ እንለምናለን። ምሕረቱንም እንጠይቀዋለን። ወደርሱ ንስሐ እንገባለን። ከነፍሳችን ክፉቶችና ከመጥፎ ሥራዎቻችንም በአላህ እንጠበቃለን። አላህ ቅኑን መንገድ የመራው ሰው የሚያጠመው የለም፣ ያጠመመውንም የሚያቀናው የለም። አጋር ከሌለው አንድ አላህ በስተቀር ሌላ አምላክ አለመኖሩን እመሰክራለሁ። ሙሐመድም መልክተኛው መሆናቸውን እመሰክራለሁ። በአክብሮት የታጀበ የአላህ እዝነትና ሠላም ለነቢዩ ለቤተሰባቸው ለባልደረቦቻቸውና በቅንነት ለተከተሏቸው ሁሉ ይድረስ።

የተውሒድ ዕውቀት ከዕውቀቶች ሁሉ የላቀና የተከበረ፣ ከሁሉም ይበልጥ ሊተሰሙት የሚገባ ዕውቀት ነው። ስለሀያሉ አላህ ስለስሞቹ፣ ስለባህሪያቱና በፍጡራን አገልጋዮቹ ላይ ስላለው መብት የሚያስተምር ዕውቀት ነውና።

ወደ ሀያሉ አላህ የሚወስደው የእምነት ጎዳና መከፈቻ ቁልፍና የሕንጋቱም መሠረት ነው ተውሒድ። በዚህ ምክንያትም ከአላህ ወደ ሰው ልጆች የተላኩ ነቢያት በሙሉ በአንድ ቃል ለዚህ ተውሒድ ጥሪ አደርገዋል። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿وما أرسلنا من قبلك من رسول إلا نوحى إليه أنه لا إله إلا أنا فاعبدون.﴾ الأنبياء:٢٥

«ከአንተ በፊትም እነሆ ከኔ ሌላ አምላክ የለምና ተገዙኝ፣ በማለት ወደርሱ የምናወርድለት ቢሆን እንጅ ከመልክተኛ አንድንም አላላክንም።»[1]

1 አል–አንቢያ /21/ : 25

አላህ (ሱ.ወ) አንድ መሆኑን ለራሱ መስክሯል። መላእክቶም ሊቃውንቶም እንደዚሁ ለአንድነቱ ምስክርነት ሰጥተዋል። ይህንኑ በማስመልከት አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿شهد الله أنه لا إله إلا هو، والملائكة وأولوا العلم قائما بالقسط لا إله إلا هو العزيز الحكيم﴾ آل عمران:١٨

«አላህ ፤ በማስተካከል የቆመ (አስተናባሪ) ሲኾን፣ ከእርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የሌለ መኾኑን መሰከረ፤ መላእክቶችና የዕውቀት ባለቤቶችም (እንደዚሁ መሰከሩ)፤ ከርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፤ አሸናፊው ጥበበኛው ነው።»[2]

የተውሒድ አስፈላጊነት እስከዚህ የላቀ ደረጃ ያለው እስከሆነ ድረስም፣ እያንዳንዱ ሙስሊም ተውሒድን ለመማርና ለማስተማር፣ በትክክል አስተንትኖ ለመረዳትና ለማመን ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። አንድ ሙስሊም ሃይማኖቱን በጠንካራ መሠረት ላይ ለመገንባት፣ አስተማማኝና እርካታ እምነት ኖሮት በእምነቱ ፍሬና በሚያስገኘው ውጤት ለመደሰት የተውሒድ ዕውቀት በትክክል ሊኖረው ይገባል።

## የእስላም ሃይማኖት

የእስላም ሃይማኖት አላህ (ሱ.ወ) ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) የላከበት፣ ሃይማኖቶችን ሁሉ ያጠቃለለበትና ለአገልጋዮቹ ያሟላበት፣ ጸጋውን ለሰዎች ያትረፈረፈበት ሃይማኖት ነው። ለሃይማኖትነት የወደደላቸውና ከርሱ በስተቀር ሌላ ሃይማኖት እርሱ ዘንድ ተቀባይ የማይሆን ሃይማኖት

2 አል- ዒምራን /3/: 18

ነው የእስላም ሃይማኖት። ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የነቢያት መደምደሚያ መሆናቸውን በማስመልከት አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ما كان محمد أبا أحد من رجالكم ولكن رسول الله وخاتم النبيين﴾ الأحزاب: ٤٠

« ሙሐመድ፣ ከወንዶቻችሁ የአንድም ሰው አባት አይደለም፣ ግን የአላህ መልክተኛና የነቢዮች መደምደሚያ ነው፣ ...»[3]

እስላም የተሟላውና አላህ ዘንድ የተወደደ ተቀባይነት ያለው ብቸኛ ሃይማኖት መሆኑን አስመልክቶም አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿اليوم أكملت لكم دينكم وأتممت عليكم نعمتي ورضيت لكم الاسلام دينا﴾ المائدة: ٣

﴿إن الدين عند الله الاسلام﴾ آل عمران:١٩

﴿ومن يبتغ غير الاسلام دينا فلن يقبل منه وهو في الآخرة من الخاسرين﴾ آل عمران:٨٥

« ዛሬ ሃይማኖታችሁን ለናንተ ሞላሁላችሁ። ጸጋዬንም በናንተ ላይ ፈጸምኩ። ለእናንተም እስላምን ከሃይማኖት በኩል ወደድኩ፣ ... »[4]

« አላህ ዘንድ (የተወደደ) ሃይማኖት እስላም ብቻ ነው፣ ...»[5]

« ከእስላም ሌላ ሃይማኖትን የሚፈልግ ሰው፣ ፈጽሞ ከርሱ ተቀባይ የለውም፣ እርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም ከከሳሪዎቹ ነው።»[6]

3 አል-አሕዛብ /33/:40
4 አል-ማኢዳ /5/:3
5 አል-ዒምራን/3/: 19
6 አል-ዒምራን/3/: 85

የሰው ልጆች በሙሉ በእስላም ሃይማኖት አማኒይነት እንዲገዙት አላህ (ሱ.ወ) ግዴታ አድርጎ ደንግጓል። ይህንኑ በማስመልከት አላህ (ሱ.ወ) ለነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿قل يا أيها الناس إني رسول الله إليكم جميعا الذي له ملك السماوات والأرض لا إله إلا هو يحيي ويميت، فآمنوا بالله ورسوله النبي الأمي الذي يؤمن بالله وكلماته، واتبعوه لعلكم تهتدون﴾ الأعراف:١٥٨

«(ሙሐመድ ሆይ!) በላቸው:- እናንተ ሰዎች ሆይ! እኔ ወደናንተ ወደ ሁላችሁም የአላህ መልክተኛ ነኝ፤ (እርሱም) ያ የሰማያትና የምድር ንግሥና ለርሱ ብቻ የኾነ ነው፤ እርሱ እንጂ ሌላ አምላክ የለም፤ ሕያው ያደርጋል፤ ይገድላልም፤ በአላህ፡ በዚያም በአላህና በቃላቶቹ በሚያምነው የማይጽፍ፡ የማያነብ ነቢይ በኾነው መልክተኛው እመኑ፤ ቅንንም መንገድ ትመሩ ዘንድ ተከተሉት።»[7]

አቡ ሁረይራን በመጥቀስ ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ውስጥ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

(والذي نفس محمد بيده لايسمع بي أحد من هذه الأمة يهودي ولا نصراني ثم يموت ولم يؤمن بالذي أرسلت به إلا كان من أصحاب النار)

«ነፍሴ በእጁ በሆነችው (አላህ) እምላለሁ፡ ከዚህ ሕዝብ ውስጥ አይሁዳዊም ይሁን ክርስትያን ስለኔ (ስለጥሪዬ) ሰምቶ፡ በተላኩበት እምነት ሳያምን የሞተ ማንኛውም ሰው ከእሳት ጓዶች (አንዱ) ይሆናል።»

---

7 አል- አዕራፍ /7/: 158

በነቢዩ ማመን ማለት ነቢዩ ያስተማሩትን ከልብ አምኖ ማረጋገጥ መቀበልና መታዘዝ ነው እንጂ እውነት ነው ብሎ መናገር ብቻ አይደለም። በዚህ ምክንያት የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) አጎት የነበሩት አቡ ጧሊብ፡ ነቢዩ የተናገሩትን ሁሉ እውነት ነው ብሎ ከመናገራቸውና ሃይማኖቱ ከሁሉም ሃይማኖት በላጭ መሆኑን ከመመስከራቸውም ጋር በነቢዩ አማኝ አልነበሩም።

እስላማዊው ሃይማኖት ቀደም ሲል በነበሩት መለኮታዊ ሃይማኖቶች ውስጥ የተጠቃለሉትን ጠቃሚ ነገሮች ሙሉ በሙሉ ያካተተ ከመሆኑም በላይ፣ በተጨማሪም ለሁሉም ዘመን ሥፍራና ሕዝብ ምቹና ጠቃሚ የመሆን ብልጫ አለው። አላህ (ሱ.ወ) ለመልክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላቸዋል:-

﴿ وأنزلنا إليك الكتاب بالحق مصدقا لما بين يديه من الكتاب ومهيمنا عليه﴾ المائدة: ٤٨

« ወደ አንተም መጽሐፉን ከበፊቱ ያለውን መጽሐፍ አረጋጋጭና በርሱ ላይ ተጠባባቂ ሲኾን በውነት አወረድን፤ ...» 8

እስላም ነሁሉም ዘመን አገርና ሕዝብ ተስማሚና አመቺ ነው ማለት በርሱ መመሪ ተ ተግ!ራዊ ማድረጉ በየትኛውም ዘመንና ሥፍራ የሕዝብን ጥቅም ከማስጠበቅ በስተቀር በፍጹም አይጻረርም ማለት ነው። ይህ ማለት ደግሞ አንዳንድ ሰዎች እንደሚፈልጉት እስላም ለሁሉም ዘመን ሥፍራና ሕዝብ ያጐበድዳል ማለት አይደለም።

እስላማዊ ሃይማኖት፣ በተገቢው መንገድና በትክክል አጥብቆ የያዘውን ሰው አላህ (ሱ.ወ) ሊያግዘውና ከሌላው በላይ ሊያደርገው ቃል የገባለት እውነተኛ ሃይማኖት ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

---

8 አል-ማኢዳህ /5/: 48

﴿هو الذى أرسل رسوله بالهدى ودين الحق ليظهره على الدين كله ولو كره المشركون﴾ الصف: ٩

﴿وعد الله الذين آمنوا منكم، وعملوا الصالحات ليستخلفنهم فى الأرض كما استخلف الذين من قبلهم، وليمكنن لهم دينهم الذى ارتضى لهم، وليبدلنهم من بعد خوفهم أمنا، يعبدوننى لايشركون بى شيئا، ومن كفر بعد ذلك فأولئك هم الفاسقون﴾ النور: ٥٥

« እርሱ ያ አጋሪዎቹ ቢጠሉም መልክተኛውን በመምሪያ (መጽሐፍ) ፤ በእውነተኛው ሃይማኖትም (በእስላምና) ፤ ከሃይማኖት ሁሉ በላይ ይፋ ሊያደርገው የላከ ነው። »[9]

« አላህ እነዚያን ከናንተ ያመኑትንና መልካም ሥራዎችን የሠሩትን፤ እነዚያ ከነርሱ በፊት የነበሩትን እንደተካ በምድር ላይ በእርግጥ ሊተካቸው፤ ለነሱም ያንን የወደደላቸውን ሃይማኖታቸውን ሊያደላድልላቸው፤ ከፍርሃታቸውም በኋላ ጸጥታን ሊለውጣቸው፤ ተስፋን ቃል ሰጥቷቸዋል፤ በኔ ምንም የማያጋሩ ሆነው ይገዙኛል፤ ከዚያም በኋላ የካደ ሰው፤ እነዚያ እነሱ አመጸኞች ናቸው። »[10]

እስላማዊው ሃይማኖት ዐቂዳና ሸሪዓ (እምነትና ድንጋጌ) ነው። በዐቂዳውም ሆነ በሸሪዓው የተሟላ ነው።

1/ የአላህን ተውሒድ (አንድነት) ያስተምራል፤ ከሺርክ (ከማጋራት) ይከለክላል።

2/ እውነት መናገርን ያዛል፤ ከውሸት ይከለክላል።

---

9 አል-ሶፍ /61/:9
10 አል- ኑር /24/: 55

3/ ፍትሕና እኩልነት እንዲሰፍን ያዛል፤ ግፍና ጭቆና ይከለክላል።[11]

4/ ለታማኝነትና ለአደራ ጠባቂነት ያዛል፤ ከካዲነትና ከእምነት አጉዳይነት ይከለክላል።

5. ለቃል ኪዳን አክባሪነት ያዛል፤ ቃል አባይነትን ይከለክላል።

6. ለወላጆች መታዘዝና በጐ አድራጊነት ያዛል፤ እነሱን ማስቀየም ይከለክላል።

7. ዝምድና እንዲቀጠል ያዛል፤ ዝምድና ማቋረጥን ይከለክላል።

8. ለመልካም ጉርብትና ያዛል፤ መጥፎ ጉርብትና ይከለክላል።

በአጠቃላይ አነጋገር እስላም በመልካም ሥነምግባራት ሁሉ ያዛል። ከመጥፎና ውዳቂ ባህርያት ሁሉ ይከለክላል።

በመልካም ተግባራት ሁሉ ያዛል፤ ከመጥፎ ተግባራት ሁሉ በጥብቅ ይከለክላል። ይህንኑ በማስመልከት አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ إن الله يأمر بالعدل والاحسان، وإيتاء ذى القربى، وينهى عن الفحشاء والمنكر والبغى يعظكم لعلكم تذكرون﴾ النحل: ٩٠

« አላህ በማስተካከል፤ በማሳመርም፤ ለዝምድና ባለቤት በመስጠትም ያዛል፤ ከአስከፊም፤ (ከማመንዘር) ፤ ከሚጠላም ነገር ሁሉ፤ ከመበደልም ይከለክላል፤ ትገነዘቡ ዘንድ ይገሥጻችኋል።»[12]

---

11 ፍትህ ማለት ተመሳሳይ የሆኑ ነገሮችን ማመሳሰል የተለያዩትን ማለያየት ነው። እንዳንድ ሰዎች የአለም ሃይማኖቶች የአሁኑን ሃይማኖት ብለው ያለገደብ በአንድነት መልኩ የሚያሳዩት ግዴታ ልዩ እኩልነት አድርገዋል። በዚህ ተፈጥሮ በተፈጥሮ ያላቸውን የሚለያዩ ነገሮችን ማመሳሰል እኩል ይሆን ያለመሆኑና አድርገውም የሚያመሳስሉት አድርገው እንጂ ፍትሕ አይደለም።

12 አል- ነሕል /16/: 90

# የእስላም ማዕዘናት (አርካኑል እስላም)

የእስላም ማዕዘናት ማለት ሃይማኖቱ የታነጸባቸው የማዕዘን መሠረቶች ማለት ነው። እነሱም ቀጥሎ በእብኑ ዑመር አማካይነት በተላለፈው ነቢያዊ ሐዲስ ውስጥ የተመለከቱት አምስት ማዕዘናት ናቸው።

(بنى الاسلام على خمسة: على أن يوحد الله (وفى روايـة) على خمس: شهادة أن لا إله إلا الله وأن محمدا عبده ورسوله، وإقام الصلاة وإيتاء الزكاة وصيام رمضان والحج) متفق عليه

« እስላም የተገነባው በአምስት ነገሮች ላይ ነው:- ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ አለመኖሩንና ሙሐመድ የአላህ አገልጋይና መልክተኛው መኾናቸውን መመስከር፣ ደንቡን ጠብቆና አዘውትሮ ሶላት መስገድ፣ ዘካት መክፈል፣ የረመዳን (ወር) መጾምና ሐጅ ማድረግ ናቸው። »[13]

## 1– ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ አለመኖሩንና ሙሐመድ አገልጋዩና መልክተኛው መሆናቸውን መመስከር

ይህ ቃለ ምስክር በፍጹምነትና በቁርጠኝነት በልብ አምኖ በመቀበል በአንደበት የሚገለጽ ምስክርነት ነው። በእርግጠኛነቱና በቁርጠኝነቱ የአይን እማኝነት ያህል ምስክርነት ተብሏል። ይህ ቃለ ምስክርነት ሁለት ክፍሎች ቢኖሩትም– ለአላህ ተውሒድና ለሙሐመድ መልክተኛነት የተሰጠ ሁለት

13 ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት ሐዲስ

ኅይነት ምስክርነት ቢሆንም– እንደ አንድ ማዕዘን ብቻ ይወሰዳል። ለዚህ ምክንያቱ አንድም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የአላህን መልክት የሚያስተላልፉ በመሆናቸው እርሳቸው የአላህ አገልጋይና መልክተኛው መሆናቸውን መመስከር፣ ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ በማረጋገጥ የተሰጠውን ቃለ ምስክርነት የሚያሟላ በመሆኑ ነው። ወይ ደግሞ ሁለቱ ቃለ ምስክርነት ሥራዎች አላህ ዘንድ ትክክለኛ ሆነው እንዲገኙና ተቀባይነት እንዲኖራቸው ለማድረግ ዋነኛው መሠረት በመሆናቸው ነው። ለአላህ (ሱ.ወ) ፍጹም ሳይሆኑና የመልክተኛውን ፈለግ ሳይከተሉ አንድ ሥራ ትክክለኛ መሆንም ሆነ ተቀባይነት ማግኘት አይችልም። ለአላህ (ሱ.ወ) ፍጹም በመሆን ከአላህ በስተቀር ሌላ አምላክ አለመኖሩን የመመስከሩ ሁኔታ ይረጋገጣል። የአላህን መልክተኛ በመከተልም ሙሐመድ የአላህ አገልጋይና መልክተኛው መሆና ቸውን የመመስከሩ ሁኔታ ይረጋገጣል።

ከዚህ ቃለ ምስክርነት አበይተ ጥቅሞች መካከል ልብና ነፍስን ከፍጡራን ባርነት ነጻ ማውጣትና ከነቢያት በስተቀር ለሌሎች ተከታይ ከመሆን ማላቀቅ ይገኙበታል።

## 2– ሰላትን አዘውትሮ መስገድ

ይህ ማለት አዘውትሮ በተሟላ ሁኔታ ሥነ ሥርዓቱንና ወቅቶቹን ጠብቆ በትጋት በመስገድ አላህን መገዛት ማለት ነው። ሰላት ከሚያስገኛቸው ጥቅሞች መካከል የልብ (የመንፈስ) እርካታና የዐይን ማረፊያ ማግኘት፣ ከመጥፎና ከሚጠሉ ነገሮች መራቅ ይገኙበታል።

## 3– ዘካት መስጠት

ዘካት ከሚከፈልባቸው የሀብት ዓይነቶች በግዴታነት የተደነገገውን የሀብት መጠን ለሚገባቸው ክፍሎች በመስጠት አላህን (ሱ.ወ) መገዛት ነው። ከጥቅሞቹ መካከል ነፍስን ከወራዳ ባህሪ– ከንፉግነት– ማጽዳትና የእስላምና የሙስሊሞችን ችግር መቅረፍ ይገኙበታል።

## 4– የረመዳንን ወር መጾም

በረመዳን ወር ቀናት ጾምን ከሚያስገድቱ ነገሮች ራስን ቆጥቦ በመዋል አላህን መገዛት ነው። ከውጤቶቹ መካከል ራስን ለአላህ (ሱ.ወ) ውዴታ ብሎ ከሚወዱት ነገሮች መቆጠብን ማለማመድ አንዱ ነው።

## 5– የሐጅ ሥርዓተ ጸሎት ማድረስ

ይህ ደግሞ ወደ ተከበረው የመካ መስጊድ በመጓዝ የሐጅ ሥርዓተ ጸሎትን በማድረስ አላህን (ሱ.ወ) መገዛት ነው።

ከውጤቶቹ መካከል የአላህን ትዕዛዝ ለመፈጸም ሲባል ኢኮኖሚያዊና አካላዊ ጥረትና መስዋትነት የመክፈል ልምድ ማስገኘት አንዱ ነው። በዚህም ምክንያት ነው ሐጅ በአላህ (ሱ.ወ) መንገድ የሚደረግ አንድ ዓይነት ትግል (ጅሃድ) የሆነው።

እነዚህ የጠቀስናቸውና ሌሎችም ያልጠቀስናቸው የማዕዘናቱ ጥቅሞችና ውጤቶች ሕዝቡን፣ በእውነተኛ ሃይማኖት ለአላህ በፍጹምነት የሚገዛ፣ ሰዎችን በፍትህና በትክክለኛነት የሚኗኗር ንጹሕና የጠራ እስላማዊ ሕዝብ ማድረግ ያስችላሉ። ከአምስቱ የኢስላም ማዕዘናት ውጭ ያሉት ሌሎች የእስላም ሕግጋት እነዚህ መሠረቶች የተቃኑ ከሆኑ የተቃኑ ይሆናሉ። የሕዝቡ አጠቃላይ አኗኗርም ሃይማኖታዊ ሁኔታዎቹ ጥሩ ሆነው ሲገኙ ይሻሻላል። ሃይማኖታዊ ጉዳዮቹ በተበላሹ መጠንም አጠቃላይ መሻሻሉ ይቀርበታል።

ይህን እንዲገለጽለት የፈለገ ሰው የሚከተለውን የአላህ (ሱ.ወ) ቃል ያንብብ:-

﴿ ولو أن أهل القرى آمنوا واتقوا لفتحنا عليهم بركات من السماء والأرض، ولكن كذبوا فأخذناهم بما كانوا يكسبون. أوأمن أهل القرى أن يأتيهم بأسنا بياتا وهم نائمون، أوأمن أهل القرى أن يأتيهم بأسنا ضحى وهم يلعبون. أفأمنوا مكر الله، فلا يؤمن مكر الله إلا القوم الخاسرون﴾ الأعراف:٩٦ - ٩٩

«የከተሞቹም ሰዎች ባመኑና በተጠነቀቁ ኖሮ፣ በነሱ ላይ ከሰማይም ከምድርም በረከቶችን በከፈትንላቸው ነበር፤ ግን አስተባበሉ፤ ይሠሩት በነበሩትም ኃጢአት ያዝናቸው። የከተሞቹ ሰዎችም እነሱ የተኙ ኾነው ቅጣታችን ሌሊት ሊመጣባቸው አይፈሩምን? የከተሞቹ ሰዎችና እነሱ የሚጫወቱ ኾነው ሳሉ፤ ቅጣታችን ቀን በረፋድ ሊመጣባቸው አይፈሩምን? የአላህንም ማዘናጋት (አለመቸኮሉ በድንገት መያዙን) አይፈሩምን? የአላህንም ማዘናጋት ከከሳራዎች ሕዝቦች በስተቀር የሚተማመን የለም።» [14]

## የእስላም ዐቂዳ መሠረቶች

ቀደም ሲል እንዳወሳነው ሁሉ የእስላም ሃይማኖት ዐቂዳ (እምነት) እና ሸሪዓ (ድንጋጌ) ነው። አንዳንድ ሕግጋቱን በመጠቆም የሸሪዓው መሠረት ተደርገው የሚቆጠሩ ግዕዛኖቹን አውስተናል።

የእስላማዊ ዐቂዳ መሠረቶች ደግሞ በአላህ፣ በመላእክቱ፣ በመጻሕፍቱ፣ በመልክተኞቹ (በነቢያቶቹ) በመጨረሻው (የትንሣኤ) ቀንና መልካምም ሆነ መጥፎ በአላህ ዕውቀትና በርሱ መሻት የሚፈጸም መሆኑን በማመን ላይ ይታነጻል። የአላህ መጽሐፍ— ቁርአንና የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ፈለገ ሕይወት ሱንና እነዚህን የእምነት መሠረቶች አመላክተዋል። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

---

14 አል-አዕራፍ /7/: 93-96

﴿ليس البر أن تولوا وجوهكم قبل المشرق والمغرب ولكن البر من ءامن بالله، واليوم الآخر، والملائكة، والكتاب والنبيين﴾ البقرة:١٧٧

«መልካም ሥራ፡ ፊታችሁን ወደ ምሥራቅና ምዕራብ አቅጣጫ ማዞር አይደለም፤ ግን መልካም ሥራ በአላህና በመጨረሻው ቀን፣ በመላእክትም፣ በመጽሐፍትም፣ በነቢያትም ያመነ ሰው፣...»[15]

﴿إنا كل شيئ خلقناه بقدر، وما أمرنا إلا واحدة كلمح بالبصر﴾ القمر: ٤٩ – ٥٠

«እኛ ሁሉን ነገር በልክ ፈጠርነው። ትእዛዛችንም እንደ ዓይን ቅጽበት አንዲት (ቃል) እንጅ ሌላ አይደለም።»[16]

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) መልአኩ ጅብሪል ስለኢማን በጠየቃቸው ጊዜ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተውታል:-

(الايمان أن تؤمن بالله، وملائكته، وكتبه، ورسله، واليوم الآخر، وتؤمن بالقدر خيره وشره) رواه مسلم

«ኢማን ማለት በአላህ፣ በመላእክቱ፣ በመጽሐፍቱ፣ በመልክተኞቹ (በነቢያቱ)፣ በመጨረሻው (የትንሣኤ) ቀን ማመንና መልካሙም ሆነ መጥፎው በአላህ መሻትና በውሳኔው የሚከሰት መሆኑን ማመን ነው። ...»[17]

በአላህ (ሱ.ወ) ማመን

በአላህ ማመን አራት ነገሮችን ያጠቃልላል:-

---

15 አል-በቀራህ /2/:177
16 አል-ቀመር /54/: 49-50
17 ሙስሊም የዘገቡት ሐዲስ

# አንደኛ– የአላህን (ሱ.ወ) መኖር ማመን

ተፈጥሮ፡ አእምሮ፡ ሸሪዓና ሕዋሳዊ ግንዛቤ የአላህን መኖር ያመለክታሉ።

1– የተፈጥሮ አስረጅነትን በተመለከተ ማንኛውም ፍጡር ቀዳሚ አሳቢና ትምህርት ሳይኖረው በተፈጥሮው በፈጣሪው የሚያምን ሆኖ ይፈጠራል። ከዚህ የተፈጥሮ ግዴታ ከጊዜ በኋላ የሚደርስ አጋጣሚ ነገር ካልጋረደው በስተቀር ከዚህ ሕግ የሚወጣ ሰው የለም። ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ይህንኑ በማስመልከት እንዲህ ብለዋል፦

( مامن مولود إلا يولد على الفطرة، فأبواه يهودانه أو ينصرانه أو يمجسانه) رواه البخارة.

« ማንኛውም የሚወለድ ሕጻን በተፈጥሮው አማኝ (ሙስሊም) ሆኖ ይወለዳል። ወላጆቹ ናቸው ክርስቲያን ወይም አይሁዳዊ ወይም እሳት አምላኪ (ዞሮስቲያን) እንዲሆን የሚያደርጉት።» [18]

2– ለአላህ መኖር የአእምሮን አስረጅነት በተመለከተ ደግሞ ያለፈውም ሆነ ያለው ፍጥረት የግዴታ ያስገኘውና የፈጠረው አምላክ የሚያስፈልገው መሆኑን እንረዳለን። ማንኛውም ፍጥረት ራሱን በራሱ ማስገኘት አይችልምና። በአጋጣሚም ሊፈጠር አይችልም። አንድ ነገር ራሱን በራሱ መፍጠር የማይችልበት ምክንያት ያ ነገር ከመገኘቱ በፊት ያልነበረ ነውና እንዴት ሆኖ ፈጣሪ ይሆናል?!

18 ቡኻሪ የዘገቡት ሐዲስ

በአጋጣሚ ሊፈጠር የማይቻልበት ምክንያት ደግሞ አንድ ድርጊት ለመከሰት የግድ-ታ አድራጊ ስለሚያስፈልግ፡ በዚህ ድንቅ ሥርዓት የተሟላ ትንብር፡ የተራቀቀ የሳቢያዎችና የውጤቶች ረቂቅ ትንጅትና በክስተቶች መካከል በሚስተዋለው አስደናቂ ትስስር ፍጥረት በአጋጣሚ እንዳልተገኘ በቁርጠኝነት ያረጋግጣሉ። በአጋጣሚ የሚከሰት ነገር መጀመሪያውኑ ቢከሰት ሥርዓት ባለው መንገድ እስካልሆነ ድረስ ከተገኘ በኋላ ለመቆየትና ለማደግ እንዴት ሥርዓትና ትንጅት ሊኖረው ይችላል? !

ስለዚህም ፍጥረታት ራሳቸውን በራሳቸው ያልፈጠሩና በአጋጣሚ የተገኙ እስካልሆኑ ደግሞ የፈጠራቸውና ያስገኛቸው የዓለማት ጌታ አላህ መሆኑ ግድ-ታ ይሆናል። አላህ (ሱ.ወ) ይህን የአእምሮ አስረጅነትና ቁርጠኛ ግረጋገጫ ሲያወሳ እንዲህ ብሏል:-

﴿أم خلقوا من غير شيئ أم هم الخالقون، أم خلقوا السموات والأرض بل لا يوقنون، أم عندهم خزائن ربك أم هم المصيطرون﴾ الطور: ٣٥ - ٣٧

« ወይስ ያለ አንዳች (ፈጣሪ) ተፈጠሩን? ወይስ እነርሱ ፈጣሪዎች ናቸውን? ወይስ ሰማያትንና ምድርን ፈጠሩን? አይደለም፤ አያረጋግጡም።ወይስ የጌታህ ግምጃ ቤቶች እነሱ ዘንድ ናቸውን? ወይስ እነሱ አሸናፊዎች ናቸውን? »[19]

ይህም ማለት ያለ ፈጣሪ አልተፈጠሩም፤ ራሳቸውን በራሳቸውም አልፈጠሩም፤ ስለዚህም ፈጣሪያቸው የዓለማት ጌታ የሆነው አላህ (ሱ.ወ) ነው ማለት ነው። ከላይ የተጠቀሱትን አንቀጾች ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሲያነቡ የሰሙት ጁበይር ብን ሙጥዕም የተባሉ ባልደረባ (ሰሐቢይ) ያን ጊዜ አልሰለሙም ነበረና :- እነዚህን አንቀጾች ከነቢዩ እንደሰሙ ልቤ

19 አጥ-ጡር /52/: 35-37

በድንጋጤና በአድናቆት ሊፈርስ ነበር፤ ያኔም ነበር እምነት ልቤ ውስጥ የተደላደለው» በማለት የተናገሩትም በዚህ እውነታ ልባቸው ስለተነካ ነበር።

ነጥቡን የሚያብራራ ምሳሌ እንስጥ። በመካከላቸው ወንዞች በሚፈሱባቸው የአትክልት ሥፍራዎች የተከበበ፣ በምንጣፎችና በአልጋዎች የተሞላና በተለያዩ ጌጣጌጦች የተሸለመ ሕንጻ ቤት አለ። ይህ ሕንጻና በውስጡ የተጠቃለሉት ግኝያዎቹ እንዲሁ በአጋጣሚ ግንም ግይሠራቸው ድንገት የተገኙ ናቸው ብሎ አንድ ሰው ቢያወራልን ወዲያውኑ ነው የምናስተባ ብለውና ወሬውን ተራ የጅላጅልነት ወሬ አድርገን የምንቀጥረው። ታዲያ መረትን ለማያትን ጠፈራዊ ምህዋሮችን ያከተተው ይህ ግዙፍ ዩኒቨርስ በዚህ ድንቅና ተአምራዊ ቅንብሩ ያለ ሠሪ ያለ አድራጊ ራሱን በራሱ ያስገኘ ወይም በአጋጣሚ የተፈጠረ ሊሆን ይችላል ተብሎ ይገመታልን?!

3– ለአላህ መኖር የሸሪዓ (የመለኮታዊ ሕግ) አስረጅነትን በተመለከተ:- መለኮታዊ መጻሕፍት በሙሉ ይህንኑ ይናገራሉ። በነዚህ መለኮታዊ መጻሕፍት (አል–ኩቱቡ–ስ–ሰማዊያህ) ውስጥ የተካተቱት ትምህርቶች የሰዎችን ጥቅም ለመጠበቅ የታለሙ መሆናቸው ራሱ ጥበበኛና የፍጡራንን ጥቅሞች በጥልቀት ዐዋቂ ከሆነ ጌታ የተላለፉ ለመሆናቸው ማስረጃ ነው። በመጻሕፍቱ ውስጥ የተጠቃለሉ ተፈጥሮያዊ እውነታዎች በነባራዊ ሁኔታ በተጨባጭ የተረጋገጡ መሆናቸውም መጻሕፍቱ የገለጿቸውን ነገሮች ማስገኘት በሚችል ቻይ ጌታ የተላለፉ ለመሆናቸው ማስረጃ ነው።

4– የሕዋሳዊ ግንዛቤ አስረጅነት ደግሞ ከሁለት አንጻር ነው።

አንደኛው:- አላህ (ሱ.ወ) የለማኞችን ልመና ሰምቶ ጸሎታቸውን ተቀብሎ ፍላጎታቸውን ሲያሟላላቸው ችግር ገጥሟቸው ሲማጸኑት በረድኤቱ ሲደርስላቸው የምንሰማና የምናየው መሆኑ ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ونوحا اذ نادى من قبل فاستجبنا له﴾ الانبياء:٧٦

«ኑሕንም ከዚያ በፊት (ጌታውን) በጠራ ጊዜ (አስታውስ)፤ ለርሱም (ጥሪውን) ተቀበልነው፤ ...»[20]

﴿ وإذ تستغيثون ربكم فاستجاب لكم﴾ الأنفال: ٩

( عن أنس بن مالك رضي الله عنه قال: إن أعرابيا دخل يوم الجمعة والنبي صلى الله عليه وسلم يخطب: فقال: ((يا رسول الله))، هلك المال، وجاع العيال، فادع الله لنا، فرفع يديه ودعا فثار السحاب أمثال الجبال فلم ينزل عن منبره حتى رأيت المطر يتحادر على لحيته. وفي الجمعة الثانية قام ذلك الاعرابي أو غيره فقال: ( هدم البناء وغرق المال فادعوا الله لنا فرفع يديه وقال اللهم حوالينا ولاعلينا، فما يشير الى إلا انفرجت)

«ከጌታችሁ ርዳታን በለመናችሁ ጊዜ፤... የተቀበላችሁን፤ (አስታውሱ)።»[21]

አንድ ጁምዓ ቀን ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ኹጥባ በሚያደርጉ ላይ እያሉ አንድ ባላገር ገባና «የአላህ መልክተኛ ሆይ! ከብትና ንብረት አለቀ፤ ልጆችም ተራቡ፤ ስለዚህ አላህ ዝናም እንዲሰጠን ጸልዩልን» አላቸው።(ነቢዩም) እጆቻቸውን ወደ ላይ ከፍ በሚያደርጉ አላህን ለመኑና ተራራ የመሰለ ደመና መታየት ጀመረ። (ነቢዩ) ድስኩሩን (ኹጥባውን) ጨርሰው ከመንበሩ ሳይወርዱ ዝናም ጺማቸው ላይ ሲንቆረቆር አየሁ። በተከታዩ ሳምንት ጁምዓ ቀንም ያ ባላገር ሰው ራሱ ወይም ሌላ ባላገር እንደዚያው ተነሳና «የአላህ መልክተኛ ሆይ! (በዝናቡ ብዛት) ቤት ፈረሰ፤ ንብረትም ተጥለቀለቀ፤ (አላህ ዝናቡን እንዲያቆም) ለምኑልን» አላቸው። (ነቢዩም) «አላህ ሆይ! በኛ ላይ ሳይሆን በአካባቢያችን አዝንበው» አሉና ወደ አንዱ አቅጣጫ በእጃቸው ሲያመለክቱ ወዲያውኑ ደመና መጥራት ያዘ በማለት አነስ ብን ማሊክን በመጥቀስ ቡኻሪ ዘግበዋል።

20 አል-አንቢያ /21/: 76
21 አል- አንፋል/8/: 9

ጸሎቱ ተቀባይነት እንዲያገኝ መሟላት ያለባቸውን መመዘኛዎች አሟልተው በፍጹምነትና በእርግጠኝነት የተማጸኑትን ሁሉ አላህ (ሱ.ወ) የሚሰጣቸው የመሆኑ ጉዳይ እስከዛሬው ዘመናችንም ድረስ የሚታይ ጉዳይ ሆኖ እንደቀጠለ ነው።

ሁለተኛው ገጽታ ደግሞ ነቢያት በትክክል ከአላህ የተላኩ ለመሆናቸው የሚሰጣቸው ከተለምዶ ውጭ የሆነውና ተአምራት (ሙዕጂዛት) ተብሎ የሚጠራው የነቢዮች ምልክትን ሰዎች አይተዋል ወይም ሰምተዋል። ይህ የነቢዮች ታእምር ነቢዮቹን ወደ ሰው ልጆች የላካቸው አላህ (ሱ.ወ) ለመኖሩ ቁርጠኛ ማስረጃ ነው። ተአምራቱ ከሰው ልጅ ችሎታ ውጭ ፡ሆኑ አላህ ለነቢያቱ እገዛና ለተልእኮአቸው ማረጋገጫ የሰጣቸው በመሆናቸው ለሰጣቸው ጌታ ሕልውና ማስረጃነታቸው የላቀ ነው።

ለዚህ ምሳሌ ለመስጠት አላህ (ሱ.ወ) ለነቢዩ ሙሳ (ዐሰ) በበትራቸው ባህሩን እንዲመቱ ሲያዛቸው መተውት ባህሩ አሥራ ሁለት ቦታ ተከፍሎ እያንዳዱ ክፍል እንደ አንድ ትልቅ ተራራ በመሆን አሥራ ሁለት ደረቅ ማሻገሪያ መንገዶች የመፈጠራቸውን ሁኔታ መጥቀስ ይቻላል። ይህንኑ ታእምራዊ ክስተት አስመልክቶ አላህ (ሱ.ወ) ቁርአን ውስጥ እንዲህ ብሏል:-

﴿فاوحينا الى موسى أن اضرب بعصاك البحر فانفلق فكان كل فرق كالطود العظيم﴾ الشعراء:٦٢

« ወደ ሙሳም ባሕሩን በበትርህ ምታው ስንል ላክንበት፤ (መታውና) ተከፈለም፤ ክፍሉም ሁሉ እንደ ታላቅ ጋራ ኾነ።»[22]

22 አሽ-ሹዐራ/27/:62

ሁለተኛ ምሳሌ ደግሞ በአላህ ፈቃድ ሙታንን በማስነሳት ከተቀበሩበት መቃብር ያስወጡ የነበሩት የነቢዩ ዒሳ (ዐሰ) ተአምር ነው። ይህንኑ አስመልክቶ አላህ (ሱ.ወ) ስለነቢዩ ዒሳ እንዲህ ብሏል:-

﴿وأحي الموتى باذن الله﴾ ال عمران:٤٩

«... በአላህም ፈቃድ... ሙታንንም አስነሳለሁ። ...»[23]

﴿وإذ تخرج الموتى بإذني﴾ المائدة: ١١٠

«... ሙታንንም በፈቃዴ (ከመቃብራቸው) በምታወጣ ጊዜ... »[24]

ሌላ ሦስተኛ ምሳሌ ለመስጠት ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ስለነቢይነታቸው ማረጋገጫ ተአምር ጨረቃ ሁለት ቦታ እንድትገመስ በማድረግ እንዲያሳዩዋቸው ቁረይሾች ሲጠይቋቸው ነቢዩ በእጃቸው ወደ ጨረቃ ሲያመለክቱ ሁለት ቦታ ተሰንጥቃ ሰዎች መመልከታቸውን መጥቀስ ይቻላል። ይህንኑ በማስመልከት አላህ (ሱ.ወ) ቁርአን ውስጥ እንዲህ ብሏል:-

﴿اقتربت الساعة وانشق القمر وان يروا آيةً يعرضوا ويقولوا
سحر مستمر﴾ القمر:١ - ٢

«ሰዓቲቱ (የትንሣኤ ቀን) ተቃረበች፤ ጨረቃም ተገመሰ፤ ታምርንም ቢያዩ (ከእምነት) ይዞራሉ፤ (ይህ) ዘውታሪ ድግምት ነውም ይላሉ።»[25]

---

23 አለ-ዒምራን /3/: 49
24 አለ-ማኢዳህ /5/: 110
25 አለ-ቀመር /54/: 1-2

አላህ የመልክተኞቹን እውነተኛነት ለማረጋገጥ ለነቢያቱ እገዛና ድጋፍ እንዲከሰቱ የሚያደርጋቸው እነዚህ ተአምራት ለአላህ (ሱ.ወ) መኖር ቁርጠኛ ማረጋገጫ ናቸው።

## ሁለተኛ – በአላህ ጌትነት ማመን

ይህ ማለት አላህ ባላንጣም ሆነ ረዳት የሌለው ብቸኛ ጌታ መሆኑን ማመን ማለት ነው። ጌታ ማለት ፈጣሪነት ንግሥናና አዛዥነት አንጡራ መብቱ የሆኑለት ጌታ ነው። ይህንኑ በማስመልከት አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ألا له الخلق والأمر﴾ الأعراف: ٥٤

﴿ذلكم الله ربكم له الملك، والذين تدعون من دونه ما يملكون من قطمير﴾ فاطر: ١٣

«... ንቁ! መፍጠርና ማዘዝ የርሱ ብቻ ነው! ...»

«... ይሃችሁ ጌታችሁ አላህ ነው፤ ንግሥናው የርሱ ብቻ ነው፤ እነዚያም ከርሱ ሌላ የምትገዟቸው፤ የተምር ፍሬ ሽፋን እንኳ አይኖራቸውም»

በልቡ የሚያምነውን የማይናገር እብሪተኛ ካልሆነ በስተቀር ከፍጡራን የአላህን (ሱ.ወ) ጌትነት ያስተባበለ ሰው መኖሩ አይታወቅም። ካልም ፈርዖን እንዳደረገው ግድነት በአፉ ብቻ – ሕሊናው አለመሆኑን እየነገረው – ጌታችሁ እኔ ነኝ የሚል ግድነት ነው የሚናገረው። ይህን የፈርዖን እብሪት ቁርአን እንደሚከተለው አስፍሯል:-

---

26 አል– አዕራፍ/7/: 54
27 ፋጢር /35/: 13

﴿أنا ربكم الأعلى﴾ النازعات:٢٤

﴿يا أيها الملأ ما علمت لكم من إله غيري﴾ القصص:٣٨

«እሱም፡- እኔ ታላቁ ጌታችሁ (የበላይ አምላካችሁ) ነኝ።»[28]

«ፈርዖንም እናንተ መኳንንቶች ሆይ! ከእኔ ሌላ ለእናንተ አምላክን ምንም አላወቅሁም! ...»[29]

ይህ አባባሉ ግን እውነቱን ከልቡ እንደዚያ መሆኑን ለሰዎችም ባይሆን ራሱን በራሱ ሊሸነግል ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿وجحدوا بها واستيقنتها أنفسهم ظلما وعلوا﴾ النمل:١٤

﴿لقد علمت ما أنزل هؤلاء إلا رب السموات والأرض بصائر وإني لأظنك يا فرعون مثبورا﴾ الاسراء:١٠٢

---

28 አል-ናዚዓት /79/: 24
29 አል- ቀሶስ /28/: 38

« ነፍሶቻቸውም ያረጋገጧት ሲኾኑ፤ በበደልና በኩራት በርሷ ካዱ፤ ... »[30]

« (ሙሳም): እነዚህን (ታምራቶች)፤ መገሠጫዎች ሲኾኑ፤ የሰማያትና የምድር ጌታ እንጂ ሌላ እንዳላወረዳቸው በእርግጥ አውቀሃል፤ እኔም ፈርዖን ሆይ፤ የምትጠፋ መኾንህን በእርግጥ እጠረጥርሃለሁ አለው።» [31]

በዚህ ምክንያትም አጋሪዎች አምልኮትን በተመለከተ ከእርሱ ጋር ባዕድ አማልክት ከመሰሏቸውም ጋር የአላህን ጌትነት ግን ያረጋግጡ ነበሩ። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ قل لمن الأرض ومن فيها إن كنتم تعلمون، سيقولون لله، قل أفلا تذكرون، قل من رب السماوات السبع ورب العرش العظيم، سيقولون لله، قل أفلا تتقون، قل من بيده ملكوت كل شيء وهو يجير ولا يجار عليه إن كنتم تعلمون، سيقولون لله قل فأنى تسحرون﴾ المؤمنون:٨٤ - ٨٩

« :- ምድርና በውስጧ ያለው ሁሉ ፤ የማን ነው? የምታውቁ ብትኾኑ ፤ (ንገሩኝ)፤ በላቸው። በእርግጥ የአላህ ነው፤ ይሉሃል፤ ታዲያ አትገሠጹምን? በላቸው። :- የሰባቱ ሰማያት ጌታና የታላቁ ዐርሽ ጌታ ማን ነው? በላቸው። በእርግጥ አላህ ነው ይሉሃል፤ እንግዲያ አትፈሩትምን? በላቸው። :- የነገሩ ሁሉ ግዛት በእጁ የኾነ፤ እርሱ የሚጠብቅ፤ በእርሱ ላይ የማይጠበቅ፤ ማ፤ ነው? የምታውቁ እንደ ኾናችሁ ፤ በእርግጥ አላህ ነው፤ ይሉሃል፤ ታዲያ እንዴት ትታለላችሁን? በላቸው።»[32]

﴿ ولئن سألتهم من خلق السماوات والأرض ليقولن خلقهن العزيز العليم﴾ الزخرف:٩

« ሰማያትንና ምድርንም ማን ፈጠራቸው ብለህ ብትጠይቃቸው፤ አሸናፊው ዐዋቂው (አላህ) በእርግጥ ፈጠራቸው ይላሉ።»[33]

30 ሱራ-ነምል /27/: 24
31 ሱራ- ኢስራእ /17/: 102
32 ሱራ-ሙእሚኑን/23/:84-89
33 ሱራ- ዙኽሩፍ /43/:9

የአላህ አዛዥነትና ጌትነት የፈጣሪነትና የደንጋጊነት ጌትነትንም ያጠቃልላል። በሻው መንገድና ጥበቡ በሚወስነው ሁኔታ የፍጥረተ ዓለሙ አስተናባሪና ፍጹማዊ ዳኛ እንደሆነ ሁሉ፣ የአምልኮ (የዕባዳ) አፈጻጸም ደንብና የበይነሰብ (ሙዓመላ) ሕጎችን ጥበቡ በሚወስነው መሠረት የሚደነግግ ብቸኛ አስተዳዳሪም ነው። ከአላህ (ሱ.ወ) ጋር የአምልኮ (የዕባዳ) ሕግን ደንጋጊ ወይም የማህበራዊ ሕይወት ግንኙነቶች አስተዳዳሪ አድርጎ ሌላ ፍጡር የያዘ ሰው በአላህ አጋርቷል፤ እምነትንም አላረጋገጠም።

## ሦስተኛ:- በአምላክነቱ ማመን

ይህ ማለት ደግሞ አጋር (ሽሪክ) የሌለው ብቸኛ አምላክ አላህ መሆኑን ማመን ማለት ነው። አምላክ ማለት ፍቅርና ክብረታ እየሰጡት የሚያመልኩበት ነገር ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿وإلهكم إله واحد لا إله إلا هو الرحمن الرحيم﴾ البقرة:١٦٣

«አምላካችሁም አንድ አምላክ ብቻ ነው፤ ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም፤ (እርሱ) እጅግ በጣም ርህሩህ አዛኝ ነው።» [34]

﴿شهد الله أنه لا إله إلا هو، والملائكة، وأولوا العلم، قائما بالقسط لا إله إلا هو العزيز الحكيم﴾ آل عمران:١٨

«አላህ በማስተካከል የቆመ (አስተናባሪ)ሲሆን ፤ ከእርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የሌለ መሆኑን መሰከረ፤ መላእክቶችና የዕውቀት ባለቤቶችም፣ (እንደዚሁ መሰከሩ)፤ ከርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፤ አሸናፊው ጥበበኛው ነው።» [35]

---

34 አል- በቀራህ /2/: 163
35 አል- ዒምራን /3/: 18

ከአላህ ጋር እንደ አምላክ ተወስደው የሚመለኩ ነገሮች ሁሉ አምላክነ ታቸው ውድቅና ሰው ሰራሽ ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ ذلك بان الله هو الحق، وان ما يدعون من دونه الباطل، وان الله هو العلي الكبير ﴾ الحج:٦٢

«ይህ፣ አላህ እርሱ እውነት በመኾኑ፣ ከእርሱ ሌላ የሚገዙት ነገር እርሱ ፍጹም ውሸት በመኾኑ፣ አላህም እርሱ የሁሉ በላይ ታላቅ በመኾኑ ነው።»[36]

እነዚህ ባዕድ አማልክት «አማልክት» መባላቸው አምላክ የመሆን መብት አያሰጣቸውም። ላት፣ ዑዛዛና መናት በሚል ስያሜ በዐረቢያ ይመለኩባቸው የነበሩትን ጣዖታት አስመልክቶ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ ان هي إلا أسماء سميتموها أنتم وآباؤكم، ما أنزل الله بها من سلطان ﴾ النجم:٢٣

«እነርሱ እናንተና አባቶቻችሁ (አማልክት ብላችሁ) የጠራችኋቸው ስሞች ብቻ እንጅ ምንም አይደሉም። አላህ በርሷ (መገዛት) ምንም ማስረጃ አላወረደም፤ ..»[37]

ነቢዩ ዩሱፍ (ዐ.ሰ) ለእስር ቤት ባልደረባቸው የተናገሩት ቁርአን ውስጥ እንደሚከተለው ሰፍሯል:-

﴿ الرباب متفرقون أم الله الواحد القهار، ما تعبدون من دونه إلا أسماء سميتموها أنتم وآباؤكم ما أنزل الله بها من سلطان ﴾

يوسف:٣٩ - ٤٠

---

36 አል- ሐጅ /22/: 62
37 አል- ነጅም /53/: 23

« ... የተለያዩ (በቁጥር ከመርት ከአንድነት የተለዩ) አምላኮች ይሻላሉን ወይስ አሸናፊው አንዱ አላህ? ከርሱ ሌላ እናንተና አባቶቻችሁ (አማልክት ብላችሁ) የሰየማችኋቸውን ስሞች እንጅ አትገዙም፤ አላህ በርሷ ምንም አስረጅ አላወረደም፤ »[38]

በዚህ ምክንያት ነው ነቢዮች (ሰ.ዐ.ወ) ለሕዝቦቻቸው የሚከተለውን አቢይ ትዕዛዝ ይናገሩ የነበሩት:-

﴿ اعبدوا الله مالكم من إله غيره ﴾ هود:٥٠

« ... አላህን ተገዙ፤ ከእርሱ ሌላ ምንም አምላክ የላችሁም፤ ... »[39]

አጋሪዎች ግን ይህን ትዕዛዝና ጥሪ እምቢ ብለው ከአላህ ጋር ባዕድ አማልክት ያዙ። የሐሰት አማልክቱን ከአላህ (ሱ.ወ) ጋር በማምለክና ከነርሱ እገዛና ረድኤት በመለመን ተማጸኗቸው።

ጣዖታውያን (ሙሽሪኮች) ለባዕድ አማልክት መገዛታቸውን ፤ አላህ (ሱ.ወ) በሁለት ሕሊናዊ ማስረጃዎች ውድቅ አድርጓል።

አንደኛው— እነዚህ ባዕድ አማልክት ምንም ዓይነት የአምላክነት መለያ የሌላቸው መሆኑ ነው። ጣዖታት ፍጡራን እንጂ መፍጠር የማይችሉ፤ ለሚያመልኳቸው ወገኖች ጥቅም የማይሰጡና ጉዳትም የማያስወግዱላቸው፤ ማንንም የማኖሩና የመግደል ሥልጣን የሌላቸው፤ ከሰማያትም ምንም የሌላቸውና ምንም የማይጋሩት ፍጡራን ናቸው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ واتخذوا من دونه آلهة لا يخلقون شيئا وهم يخلقون. ولايملكون لأنفسهم ضرا ولا نفعا ولا يملكون موتا ولا حياة ولا نشورا ﴾ الفرقان:٣

38 ዩሱፍ (12)፡ 39–40
39 ሁድ (11)፡ 50

﴿قل ادعوا الذين زعمتم من دون الله لا يملكون مثقال ذرة فى السملوات ولا فى الأرض وما لهم فيهما من شرك، وما له منهم من ظهير ولا تنفع الشفاعة عنده إلا لمن أذن له﴾ سبأ: ٢٢ - ٢٣

﴿أيشركون ما لا يخلق شيئا وهم يخلقون. ولا يستطيعون لهم نصرا ولا أنفسهم ينصرون﴾ الأعراف: ١٩١ - ١٩٢

«(ከሐዲዎች) ከርሱ ሌላ፣ ምንንም የማይፈጥሩን፣ እነሱም የሚፈጠሩን፣ ለነፍሶቻቸውም ጉዳትን ለመከላከል ጥቅምንም ለማምጣት የማይችሉን፣ ሞትንና ሕይወትንም፣ መቀስቀስንም የማይችሉን አማልክት ያዙ።»[40]

«እነዚያን ከአላህ ሌላ (አማልክት ብላችሁ) የምታስቧቸውን ጥሩ፤ በሰማያትም በምድርም ውስጥ የብናኝ ክብደት ያክል ምንንም አይችሉም፤ ለእነርሱም በሁለቱም ውስጥ ምንም ሽርክና የላቸውም፤ ከእነርሱም ለርሱ ደጋፊ አጋዥ የለውም በላቸው።»[41]

«ምንንም የማይፈጥሩትንና እነርሱም የሚፈጠሩትን (ጣዖታት) ያጋሩታልን? ለእነርሱም መርዳትን የማይችሉትን፣ ነፍሶቻቸውንም የማይረዱትን፤ (ያጋሩታልን)»[42]

የአማልክቱ ትክክለኛ ሁኔታ ይህን የመሰለ ከሆነ ዘንዳ በእርሱ ማምለክ የከፋ ጅልነትና የከፋ ስህተት ነው።

ሁለተኛ- እነኛ ሙሽሪኮች (መሻሪኮች) ለአላህ (ሱ.ወ) እርሱ ብቻ ሊገባ ሃቁ የሆነውም ነገር ሥልጣን በእጁ የሆነ፤ እርሱ የሚያመልኩ ለሌላ ግን በርሱ የሚጠበቅ የሆነ ሃቁ መሆኑን ያረጋግጣሉ። ይህ አድማቸው ራሱ በአምልኮትም እርሱን ብቻ እንዲያመልኩና እንዲገዙት፤ — ግዴታን

40 አል- ፉርቃን /25/:3
41 ሰበእ /34/: 22-23
42 አል- አዕራፍ /7/: 191-192

እንዲረጋገጡ ሁሉ ብቸኛ አምላክነቱንም እንዲያረጋግጡ ያስገድዳቸዋል።

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿يا أيها الناس اعبدوا ربكم الذى خلقكم والذين من قبلكم لعلكم تتقون، الذى جعلكم الأرض فراشا والسماء بناء وأنـزل من السماء ماء فأخرج به من الثمرات رزقا لكم فلا تجعلوا لله أندادا وأنتم تعلمون﴾ البقرة:٢١ - ٢٢

﴿ولئن سألتهم من خلقهم ليقولن الله فأنى يؤفكون﴾ الزخرف:٨٧

﴿قل من يرزقكم من السماء والأرض أم من يملك السمع والأبصار ومن يخرج الحي من الميت ويخرج الميت من الحي ومن يدبر الأمر فسيقولون الله، فقل أفلا تتقون، فذلكم الله ربكم الحق، فماذا بعد الحق إلا الضلال فأنى تصرفون﴾ يونس:٣١ - ٣٢

« እናንተ ሰዎች ሆይ! የፈጠራችሁን፣ እነዚያንም ከናንተ በፊት የነበሩትን (የፈጠረውን) ጌታችሁን ተገዙ፤ (ቅጣትን) ልትጠነቀቁ ይከጀላልና። (እርሱ) ያ ለናንተ ምድርን ምንጣፍ፣ ሰማይንም ጣራ ያደረገ ነው፤ ከሰማይም፣ (ከደመና) ውሃን ያወረደ፣ በርሱም ከፍሬዎች ለናንተ ሲሳይን ያወጣ ነው፤ እናንተም (ፈጣሪነቱን) የምታውቁ ስትሆኑ፣ ለአላህ ባላንጣ ዎችን አታድርጉ።» [43]

« ማን እንደፈጠራቸውም ብትጠይቃቸው፤ በእርግጥ አላህ ነው፤ ይላሉ። ታዲያ (ከእምነት) ወዴት ይዞራሉ።» [44]

« ከሰማይና ከምድር ሲሳይን የሚሰጣችሁ ማን ነው? መስሚያዎችንና ማያዎችንስ የፈጠረ ማን ነው? ከሙትም ሕያውን፣ የሚያወጣ ከሕያውም ሙትን የሚያ ወጣስ ማን ነው? ነገሩን ሁሉ የሚያስተናብርስ ማን ነው? በላቸው፤ በእርግጥም አላህ ነው ይሉሃል፤ ታዲያ (ለምን ታጋራላችሁ?) አትፈሩትምን? በላቸው። ይሃችሁም እውነተኛ ጌታችሁ አላህ ነው፤ ከእውነትም በኋላ ጥመት እንጂ ሌላ ምን አለ? (ከእውነት) እንዴት ትዞራላችሁ?» [45]

---

43 አል- በቀራህ /2/:21 – 22
44 አል-ዙኽሩፍ /43/: 87
45 ዩኑስ /10/: 431–32

# አራተኛ – በአላህ ስሞችና በባህርያቱ ማመን

ይህ ማለት አላህ (ሱ.ወ) ቁርአን ውስጥ ወይም በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሱንና ውስጥ ለራሱ ያረጋገጣቸውን ስሞችና ባህርያትን ለርሱ ተገቢ በሆነ መልኩ ምንም ሳያዛቡ፣ ትርጉም አልባ ሳያደርጉ፣ ከፍጡራን ጋር ሳያመሳስሉና ትክክለኛ አኳኋናቸው እንዲህ ነው ሳይሉ ማረጋገጥ ማለት ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ولله الأسماء الحسنى فادعوه بها وذروا الذين يلحدون فى أسمائه سيجزون ما كانوا يعملون﴾ الأعراف: ١٨٠

﴿وله المثل الأعلى فى السماوات والأرض، وهو العزيز الحكيم﴾ النحل: ٦٠

﴿ليس كمثله شيء وهو السميع البصير﴾ الشورى: ١١

« ለአላህም መልካም ስሞች አሉት፤ (ስትጸልዩ) በርሷም ጥሩት፤ እነዚያንም ስሞቹን የሚያጣምሙትን ተውዋቸው፤ ይሠሩት የነበሩትን ነገር በእርግጥ ይመነዳሉ።»[46]

« ... ለአላህም ታላቅ ባሕርይ አለው፤ እርሱም አሸናፊው ጥበበኛው ነው።»[47]

« ... የሚመስለው ምንም ነገር የለም፤ እርሱም ሰሚው ተመልካች ነው።»[48]

በዚህ ጉዳይ ላይ ሁለት ቡድኖች ከትክክለኛው መንገድ ጠመዋል:-
<u>አንደኛው ቡድን</u>– የአላህን ስሞችና ባህርያት በሙሉ ወይም በከፊል ችላ ብለው ያስተባበሉና ትርጉም አልባ ያደረጉ ወገኖች (አልሙዐጢላ) ናቸው።

---

46 አል-አዕራፍ /7/: 180
47 አል-ነሕል /16/: 60
48 አል-ሹራ /42/: 11

ይህ ቡድን ስሞቹንና ባህርያቱን አረጋግጦ መቀበሉ አላህን (ሱ.ወ) ከፍጡራን ጋር ማመሳሰልን ያስከትላል በሚል ነው የማይቀበለው። ይህ አባባል ግን በተለያዩ አንጻሮች ውድቅ ነው። ከነዚህም:-

አንደኛ– የአላህ (ሱ.ወ) ንግግር እርስ በርሱ ይቃረናል ማለትን የመሰለ የተሳሳተ ውጤት ላይ እንዲደረስ ያደርጋል። አላህ (ሱ.ወ) ስሞችና ባህርያት እንዳሉት ለራሱ አረጋግጦ ምንም ነገር እርሱን የማይመስል መሆኑን ገልጸአል። ስለዚህም ስሞቹንና ባህርያቱን አረጋግጦ መቀበሉ እርሱን ከፍጡራን ጋር ከማመሳሰል ውጤት ላይ እንዲደረስ የሚያደርግ ቢሆን ኖሮ የአላህ ንግግር እርስ በራሱ ይጋጫል፤ አንዱ ሌላውን ያስተባብላል ማለት በሆነ ነበር።

ሁለተኛ– በአንድ ስም ወይም ባህርይ ውስጥ የሁለት ነገሮች መጣመር የግድ ተመሳሳዮች እንዲሆኑ አያደርግም። ሁለት ግለሰቦች ብንወስድ ሁለቱም የሚናገር የሚሰማና የሚያይ ሰው ከመሆናቸው አንጻር አንድ ዐይነት መሆናቸውን እንረዳለን። ይህ ማለት ግን ሁለቱ ግለሰቦች የግድ በስብእናቸው፣ ሰሚ ተመልካችና ተናጋሪ ከመሆን ባህርያቸው ሙሉ በሙሉ ይመሳሰላሉ ማለት አይደለም። እንስሳት እጆች እግሮችና ዐይኖች እንዳሏቸው እናውቃለን። በነዚህ ነገሮች አንድ ዐይነት በመሆናቸው ብቻ የግድ ተመሳሳይ እጆች እግሮችና ዐይኖች አሏቸው ማለት አይደለም።

ፍጡራን በአጠቃላይ መልኩ በሚኖራቸው የጋራ ስሞችና ባህርያት የሚለያዩ መሆናቸው ግልጽ ከሆነ ዘንዳ በፈጣሪና በፍጡራን መካከል ያለው ልዩነት ከሁሉም በላይ ሰፊና ከፍተኛ ልዩነት መሆኑ ግልጽ ይሆናል።

<u>ሁለተኛው ቡድን</u>– የአመሳሳዮች (አህል ሙሸብባህ) ቡድን ነው። ይህ ቡድን ደግሞ የድንጋጌ አንቀጾቹ ግልጽ ትርጉም (ዟሂር) የሚያመለክተው ነው በሚል አባባል የአላህን ስሞችና ባህርያቱን ከፍጡራን ጋር ከማመሳሰል ጋር አረጋግጠው የሚቀበል ቡድን ነው። አላህ (ሱ.ወ) ባሮቹን የሚያናግረው መረዳትና መገንዘብ በሚችሉበት መንገድ ብቻ ነውና አንቀጾቹን የምንረዳው ከፍጡራን ስሞችና ባህርያት በማነጻጸር ነው የሚል አቋም አላቸው። ይህ አቋም በተለያዩ አንጻር ሲታይ ውድቅና ስህተት ነው። ከነዚህም:-

አንደኛ– አላህን (ሱ.ወ) ከፍጡራት ጋር ማመሳሰል አእምሮና ሸሪዓ (ሕግ) የማይቀበለው ጉዳይ ነው። የቁርአንና የነቢዩ ሐዲስ አንቀጾች (ኑሱስ) ደገሞ ውድቅ ነገር መሆን አይችሉም።

ሁለተኛ– አላህ (ሱ.ወ) ባሮቹን የሚያናግረው ከመሠረታዊ ትርጓሜው አንጻር መረዳት በሚችሉት ሁኔታ ነው። ከአጠቃላይ ትርጉሙ ውጭ የተጓላ ምንነቱንና አኳኋኑን በተመለከተ ግን ከአላህ ስሞችና ከባህርያቱ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን የሚጠቅሱ አንቀጾች ትርጉም ፍጹማዊ ምንነትና አኳኋን የሚያውቀው አላህ ብቻ ነው።

አላህ (ሱ.ወ) ራሱን በሰሚነት ሲገልጽ፡ ሰሚነት ከአጠቃላይ ትርጉሙ አንጻር (ድምጽን መስማት ነውና) ግልጽ ነው። የአላህን (ሱ.ወ) ሰሚነት በተመለከተ ግን ትክክለኛ ትርጉሙና አኳኋት አይታወቅም። የመስማት ባህርይ ትክክለኛ ገንዛቤ በፍጡራን መካከል እንኳ ቢሆን የሚለያይ በመሆኑ በፈጣሪና በፍጡራን መካከል ያለው የመስማት ልዩነት እጅግ የሰፋና ከፍተኛ የሆነ ፍጹማዊ ልዩነት ነው።

አላህ (ሱ.ወ) ከዐርሹ (ከዙፋኑ) በላይ መደላደሉን ሲናገር፡ መደላደል (እስትዋ) ማለት ከመሠረታዊ ትርጉሙ አንጻር ይታወቃል። የርሱን በዐርሹ ላይ መደላደል (እስትዋ) በተመለከተ ግን ትክክለኛ ምንነቱ አኳኋኑና ፍጹማዊ ትርጉሙ አይታወቅም። ፍጡራንን በተመለከተ እንኳ መደላደል የሚለው ባህርይ ይለያያልና። በወንበር ላይ መደላደልና በሚበረገግ አስቸ ጋሪ ገመል ጀርባ ላይ በመደላደል መካከል ግልጽ ልዩነት አለ። በፍጡራን መካከል ራሱ ልዩነት ያለው መሆኑ ከታወቀ ደግሞ በፈጣሪና በፍጡራን መደላደል መካከል ያለው ልዩነት እጅግ በጣም ሰፊና ፍጹማዊ ልዩነት ነው።

ከዚህ በላይ በገለጽነው መንገድ በአላህ (ሱ.ወ) ማመን ለምዕመናን ታላላቅ ውጤቶች የሚያስገኝ ሲሆን ከውጤቶቹ መካከል የሚከተሉትን እናገኛለን:-

አንደኛ– የሚፈልጉትን ከርሱ ብቻ ለማግኘት በርሱ ብቻ ላይ ተስፋ በመጣልም ሆነ እርሱን ብቻ በመፍራት ከርሱ በስተቀር ሌላ ባለማምለክ የአላህን (ሱ.ወ) አንድነት (ተውሒድ) ማረጋገጥ፣

ሁለተኛ– ከመልካም ስሞቹና ከላቁ ባህሪያቱ ይዘት አንጻር አላህን በተሟላ ሁኔታ መውደድና ማክበር፣

ሦስተኛ– አላህ ያዘዘውን በመፈጸምና ከከለከለው በመታቀብ አምልኮትን (ዕባዳን) ለርሱ ብቻ ማረጋገጥ፣

## በመላእክት (በመላእኮች) ማመን

መላእኮች በሕዋሳዊ ግንዛቤ ሥር ከሚውለው ዓለም ውጭ የሆኑ፡ አላህን የሚገዙ ምንም ዓይነት የጌትነትና የአምላክነት ባህሪ የሌላቸው፡ አላህ (ሱ.ወ) ከብርሃን ፈጥሮአቸው ለትዕዛዞቹ በፍጹምነት የመመራትና የመተግበር ኃይል የሰጣቸው ፍጡራን ናቸው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ومن عنده لا يستكبرون عن عبادته ولا يستحسرون، يسبحون الليل والنهار لا يفترون﴾ الأنبياء:١٩ - ٢٠

« ... እርሱ ዘንድ ያሉትም (መላእክት) እርሱን ከመገዛት አይኮሩም፣ አይሰለቹምም። በሌሊትና በቀንም ያወድሱታል፤ አያርፉም።»[49]

ቁጥራቸውንና ብዛታቸውን ከአላህ (ሱ.ወ) በስተቀር የሚያውቅ የለም። በቡኻሪና ሙስሊም ከአነስ በተዘገበው የነቢዩ (ሰ.ሀ.ወ) የሰማይ ዕርገት (ምዕራጅ) ሐዲስ ውስጥ እንደተረጋገጠው፡ ነቢዩ (ሰ.ሀ.ወ) በሰማይ ያለው የደመቀ ቤት (በይቱል መዕሙር) ተገልጾላቸው በየቀኑ እቤቱ ውስጥ ሰባ

49 አንቢያ /21/: 19-20

ሸህ መላእኮች የሚሰግዱበት መሆኑንና እነሱ ከወጡ በኋላ ዳግም ሳይመለሱ በዚያው የሚቀሩ ሲሆን ሌላ ሰባ ሺዎች በተከታታይ የሚሰግዱበት መሆኑና ሂደቱ ለዘለዓለሙ በዚህ የሚቀጥል መሆኑን ተናግረዋል።

## በመላእክት ማመን አራት ነገሮችን ያጠቃልላል

አንደኛ– መኖራቸውን (ሕልውናቸውን) ማመን፣

ሁለተኛ– በተለይ ስማቸውን ባወቅነው እንደ ጅብሪል ባሉት ማመንና ስማቸውን በማናውቃቸው ደግሞ መኖራቸውን በአጠቃላይ ማመን፤

ሦስተኛ– በባህርያቸው (ስፋት) ያወቅናቸውን በተነገረን መሠረት ማመን፡ ጅብሪልን በተፈጥሮ ገጽታው ስድስት መቶ ክንፎች ያሉትና ከአድማስ እስከ አድማስ የሞላ ሆኖ ያዩት መሆናቸውን ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ስለነገሩን በዚህ ማመን፤

መልአክ በአላህ (ሱ.ወ) ትዕዛዝ ወደ ወንድ ቅርጽ ሊለወጥ ይችላል። አላህ (ሱ.ወ) ጅብሪልን ወደ መርየም ሲልከው ትክክለኛ ሰው ሆኖ እንደተመሰለላት ዓይነት። ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ከሰሐቦች ጋር እንደተቀመጡ በጣም ነጭ ልብስ የለበሰ በጣም ጥቁር ጸጉር ያለው ምንም ዓይነት የመንገደኝነት ድካም የማይታይበትና ከሰሐቦቹ መካከል ማንም የማያውቀው ሰው ዓይነት ተመስሎ መጥቶ ጉልበቱን ከነቢዩ ጉልበት አስጠግቶ መዳፎቹን በጭኖቹ ላይ አድርጐ ስለ እስላም ስለ እምነት (ኢማን) ስለደግነት (ኢሕሳን) ስለትንሣኤና ስለምልክቶቹ ነቢዩን ጠይቋቸዋል።

ነቢዩም (ሰ.ዐ.ወ) ምላሽ ከሰጡት በኋላ ተነስቶ ሄደ። ከሄደ በኋላ ይህ ጅብሪል ነው ሃይማኖታችሁን ሊያስተምራችሁ ነው የመጣው በማለት ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ለሰሐቦቹ መናገራቸውን ሙስሊም ዘግበዋል።

አላህ (ሱ.ወ) ወደ ነቢዩ ኢብራሂምና ወደ ነቢዩ ሉጥ የላካቸው መላእክት በወንድ ሰው የተመሰሉ ነበሩ።

አራተኛ– አላህን ማጥራት (ተስቢሕ)፡ ቀንና ሌሊት ያለመሰላቸትና ያለ ድካም አላህን መገዛት የመሳሰሉ የአላህ ትዕዛዞችን የመፈጸም ተግባር የመሳሰሉ የምናውቃቸው ተግባራት እንዳላቸው ማመን፡

አንዳንዶቻቸው የተለየ ተግባር ሊኖራቸው ይችላል። ለምሳሌ ጅብሪል አላህ (ሱ.ወ) ወደ ነቢያትና ወደ መልክተኞች የሚያስተላልፈውን መልእክት በታማኝነት የማድረስ ተግባር አለው።

ሚካኢል በዝናምና በዕጽዋት ጉዳይ ላይ የተመደበ ነው። እስራፊል በትንሣኤው ቀንና ሰዎች ዳግም ከሞት ተቀስቅሰው ሲነሱ መለከት በመንፋት ላይ የተመደበ ነው። መለከ ሞት ሰው ሲሞት ነፍሱን በመውሰድ ላይ የተመደበ ነው። መለክ ገሀነምም እንደዚሁ በእሳተገሐነም ላይ የተወከለ ነው። ማህጸን ውስጥ ባሉት ጽንሶች ላይ የተመደቡ መላእኮች፤ አንድ ሕጻን ተጸንሶ አራት ወር ሲሞላው አላህ (ሱ.ወ) መላእካ ይልክበትና ሲሳዩን ዕድሜውን ሥራውን መናጢ ወይም ዕድለኛ መሆኑን እንዲጽፍ ያዝዋል። የሰው ልጆችን ሥራዎች መዝግበው የሚይዙ መላእኮች፤ ለያንዳንዱ ሰው ሁለት መላእኮች ከግራና ከቀኙ ተመድበው ሥራዎቹን ይመዘግባሉ። አንድ ሰው ከተቀበረ በኋላ መቃብሩ ውስጥ ሁለት መላእኮች ጌታው፡ ማን እንደሆን ሃይማኖቱና ነቢዩ ማን እንደሆን ይጠይቁታል። በመላእኮች ማመን ታላላቅ ውጤቶችን የሚያስገኝ ሲሆን ከነዚህም የሚከተሉት ይገኛሉ፡-

አንደኛ– የአላህን (ሱ.ወ) ታላቅነት፤ ኃያልነቱንና ሥልጣኑን ማወቅ፤ የፍጡር ታላቅነት የፈጣሪውን ኃያልነት ያመለክታልና።

ሁለተኛ– አላህ (ሱ.ወ) ለሰው ልጆች የሚጠብቋቸውን፡ ሥራዎቻቸውን የሚመዘግቡና ለሌሎች ጥቅሞቻቸው የተሰለፉ መላእኮችን በመመደብ ለለገሳቸው እንክብካቤ ምሥጋና ለአላህ ማድረስ፤

ሦስተኛ– አላህን (ሱ.ወ) በመገዛት በሚፈጽሙት ተግባር መላእኮችን መውደድ፤

አንዳንድ ወገኖች መላእኮች አካላት መሆናቸውን አስተባብለው፡ መላእኮች በፍጥረታት ውስጥ የሰረጸ የደግነትና የክፋት መገለጫ ኃይላት

ናቸው ይላሉ። ይህ አባባል የአላህን መጽሐፍ የነቢዩን(ሰ.ዐ.ወ) ሱንና እና የሙስሊሞችን የጋራ አቋም (እጅማዕ) የሚያስተባብል አቋም ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿الحمد لله فاطر السماوات والأرض جاعل الملائكة رسلا أولي أجنحة مثنى وثلاث ورباع﴾ فاطر:١

﴿ولو ترى إذ يتوفى الذين كفروا الملائكة يضربون وجوههم وأدبارهم﴾ الأنفال:٥٠

﴿ولو ترى إذ الظالمون في غمرات الموت والملائكة باسطوا أيديهم أخرجوا أنفسكم﴾ الأنعام:٩٣

« ምስጋና ሰማያትንና ምድርን ፈጣሪ፣መላእክትን ባለ ሁለት ሁለት፤ ባለ ሦስት ሦስትም፣ ባለ አራት አራትም ክንፎች የሆኑ መልክተኞች አድራጊ ለሆነው አላህ ይገባው፤ ...»[50]

« እነዚያንም የካዱትን፣ መላእክት ፊቶቻቸውንና ጀርባዎቻቸውን እየመቱ የቃጠሎንም ስቃይ ቅመሱ (እያሉ) በሚገድሏቸው ጊዜ ብታይ ኖሮ፤ (አስደንጋጭን ነገር ታይ ነበር)። »[51]

« ... በደለኞችንም በሞት መከራዎች ውስጥ በሆኑ ጊዜ መላእክት እጆቻቸውን ዘርጊዎች ኾነው (ለትጠጥበ) ነፍሶቻችሁን አውጡ፤ .. (የሚሏቸው ሲኾኑ) ብታይ ኖሮ፤ ( አስደናቂን ነገር ባየህ ነበር)።» [52]

﴿حتى إذا فزع عن قلوبهم قالوا ماذا قال ربكم قالوا الحق، وهو العلي الكبير﴾ سبأ:٢٣

50 ፋጢር /35/:1
51 አል- አንፋል: 50
52 አል- አንዓም /6/:93

﴿ والملائكة يدخلون عليهم من كل باب، سلام عليكم بما صبرتم، فنعم عقبى الدار ﴾

( إذا أحب الله العبد نادى جبريل أن الله يحب فلانا فأحبه، فيحبه جبريل، فينادى جبريل فى أهل السماء، ان الله يحب فلانا فأحبوه، فيحبه أهل السماء، ثم يوضع له القبول فى الأرض)

« ከለቦቻቸው ላይ ድንጋጤው በተገለጠም ጊዜ፡ (ተማላጆቹ) ጌታችሁ ምን አለ? ይላሉ፤ (አማላጆቹ) እውነትን አለ፤ እርሱም ከፍተኛው ታላቁ ጌታ ነው፣ ይላሉ።»[53]

« ... መላእክትም በነሱ ላይ ከየደጃፉ ሁሉ ይገባሉ። ሰላም ለናንተ ይሁን (ይህ ምንዳ). በመታገሳችሁ ነው፡ የመጨረሻይቱም አገር ምን ታምር ! ይሏቸዋል።»[54]

አቡ ሁረይራን በመጥቀስ ቡኻሪ በዘገቡት የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሐዲስ ውስጥም የሚከተለውን እናገኛለን:-

« አላህ አንድ ባሪያውን ሲወድ አላህ እገሌን ይወደዋልና አንተም ውደደው በማለት ለጅብሪል ያስታውቃል፡ ጅብሪልም ይወደዋል። ጅብሪል የሰማይ ነዋሪዎችን ይጣራና አላህ እገሌን ይወደዋልና እናንተም ውደዱት ይላቸዋል። የሰማይ ነዋሪዎችም ይወዱታል። ከዚያም መሬት ላይ ተቀባይነት ያገኛል።»

« ዐርብ ቀን መጀመሪያ ለጁምዓ ሰላት ወደ መስጊድ የሚሄዱትን በቅደም ተከተላቸው መሠረት የሚመዘግቡ መላእኮች በያንዳንዱ የመስጊድ በር ላይ ይቆማሉ። ኢማሙ ለኹጥባ መንበር ላይ ሲቀመጥ መዝገባቸውን ይዘጉና ቁርአን (ውዱሴ) ለማዳመጥ መጥተው ይቀመጣሉ።»

እነዚህ ቁርአናዊ አንቀጾችና ነቢያዊ ሐዲሶች መላእኮች ጠማሞቹ እንሚሉት መንፈሳዊ ኃይሎች ሳይሆኑ አካላት ለመሆናቸው ግልጽ ማስረጃ ናቸው። በነዚሁ አንቀጾች መሠረት ላይም ሙስሊሞች አንድ ወጥ የጋራ አቋም ወስደዋል።

---

53 ሰበእ /34/ : 23
54 አል- ረዕድ/13/: 23-24

## በመጻሕፍት (በኪታቦች) ማመን

በመጻሕፍት ማመን ማለት አላህ (ሱ.ወ) ለፍጡራን ባለው፣ርህራኄ ሰዎች ቅኑን መንገድ ተመርተው ለዛሬዋ ዓለም ሕይወትና ለነገዋ ዘለዓለማዊት ሕይወት ተድላ ይበቁ ዘንድ በመልክተኛ ነቢዮች አማካይነት ባስተላለፋቸው መለኮታዊ መጻሕፍት ማመን ማለት ነው።

በመጻሕፍት ማመን አራት ጉዳዮችን ያካትታል:-

አንደኛ– በትክክል ከአላህ የተወረዱ (የተላለፉ) መሆናቸውን ማመን፤

ሁለተኛ– ከነዚህ መጻሕፍት መካከል ለነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) በተላለፈው በቁርአን፡ ለነቢዩ ሙሣ (ሰ.ዐ.ወ) በተላለፈው ተውራት (ኦሪት)፡ ለነቢዩ ዒሳ (ሰ.ዐ.ወ) በተላለፈው በእንጂል (ወንጌል) እንደ ዚሁም ለነቢዩ ዳውድ (ሰ.ዐ.ወ) በተሰጠው ዘቡር (መዝሙር) በመላሰሉት

ስማቸውን በተለይ በምናውቀው ግመንና ስማቸውን በማናውቃቸው ደግሞ በአጠቃላይ መልኩ ግመን፤

ሦስተኛ– ትክክለኛ ለነዳፂነት ያላቸውን ይዞታቸውን እንደ ቁርአን የተረጋገጠውንና ከቀደሙት መጻሕፍት መካከል ያልተለወጠውን ያልተዛባ ውንና ያልተከለከለውን ክፍል ማረጋገጥ፤

አራተኛ– ያልተሻረ ሕግጋቱን መተግበር፤ ምስጢሩንና ጥቅሙን ብናውቅም ባናውቅም ወደን መቀበል፤ ከቁርአን በፊት የነበሩት መለኮታዊ መጻሕፍት በሙሉ በቁርአን ተሽረዋል። ይህንኑ በማስመልከት አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ وأنزلنا إليك الكتاب بالحق مصدقا لما بين يديه من الكتاب ومهيمنا عليه﴾ المائدة:٤٨

« ወደ አንተም መጽሐፉን ከበፊቱ ያለውን መጽሐፍ አረጋጋጭና በርሱ ላይ ተጠባባቂ ሲኾን በእውነት አወረድን፤..»[55]

ይህ ማለት ከቀደሙት መለኮታዊ መጻሕፍት ሕግጋት ውስጥ ትክክለ ኛነቱ ተረጋግጦ በቁርአን የጸደቀ እስካልሆነ ድረስ አንዱንም ተግባራዊ ማድረግ አይፈቀድም ማለት ነው።

በመጻሕፍት ማመን ከሚያስገኛቸው ታላላቅ ውጤቶች መካከል የሚከተ ሉትን እናገኛለን:-

አንደኛ– አላህ (ሱ.ወ) ለያንዳንዱ ሕዝብ የሚመራበት መጽሐፍ ማስተላለፉ ለፍጡራን ዋርቹ ያለውን ትኩረት ማወቅ፤

---

55 አል-ማኢዳ /5/:48

ሁለተኛ– አላህ (ሱ.ወ) ለያንዳንዱ ሕዝብ ከሁኔታው ጋር የሚጣጣም መጽሐፍት በመስጠቱ ውስጥ የሚንጸባረቀውን የላቀ ጥበቡን ማወቅ፤ ይህንን በማስመልከት አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

﴿لكل جعلنا منكم شرعة ومنهاجا﴾

« ... ከናንተ ለሁሉም ሕግንና መንገድን አደረግን፤ ...» [56]

ሦስተኛ ይህን ሁሉ ለለገሰ አላህ ምስጋና ማቅረብ፤

---

56 አል– ማኢዳ /5/: 48

## በመልክተኞች (በሩሱል) ማመን

መልክተኛ ማለት ከአላህ ዘንድ የተላለፈ ሕግን (ሸሪዓ) ለሰው ልጆች እንዲያደርስ የታዘዘ ነቢይ ነው። «ረሱል» መልክተኛ ማለት ሲሆን «ሩሱል» መልክተኞች ማለት ነው። የመጀመሪያው ረሱል ነቢዩ ኑሕ ሲሆኑ የመጨረሻው ረሱል ደግሞ ነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ናቸው።

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿إنا أوحينا إليك الكتاب، كما أوحينا الى نوح والنبيين من بعده﴾ النساء:١٦٣

« እኛ ወደ ኑሕና ከርሱ በኋላ ወደነበሩት ነቢያት እንዳወረድን፣ ወደ አንተም አወረድን፣...»[57]

ቡኻሪ እነስ ብን ማሊክን ጠቅሰው በዘገቡት የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሐዲስ ውስጥም የሚከተለውን እናገኛለን:-

---

57:አል-ኒሳእ /4/:163

( أن النبي صلى الله عليه وسلم ذكر ان الناس يأتون إلى ادم ليشفع لهم فيعتذر إليهم، ويقول: ائتوا نوحا اول رسول بعثه الله...)

«በትንሣኤው ቀን ሰዎች አላህን እንዲያማልዱላቸው ወደ አደም ሲመጡ አለመቻላቸውን ይቅርታ የጠየቀና አላህ መልክተኛ (ረሱል) አድርጎ መጀመሪያ ወደ ባሪያዎቹ ወደ ኑሕ ሂዱ ይላል፡ ...»

ነቢዩ ሙሐመድ(ሰ.ዐ.ወ) የነቢያት መደምደሚያ መሆናቸውን ሲገልጽ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ ما كان محمد أبا أحد من رجالكم ولكن رسول الله وخاتم النبيين﴾ الأحزاب: ٤٠

« ሙሐመድ፡ ከወንዶቻችሁ የአንድም ሰው አባት አይደለም፤ ግን የአላህ መልክተኛ፡ የነቢያት መደምደሚያ ነው፤ ...» [57]

ራሱን የቻለ ሕግ (ሸሪዓ) ይዞ ከአላህ (ሱ.ወ) የሚላክ መልክተኛ (ረሱል) የሌለው ሕዝብ አልነበረም። ወይም ከበፊቱ የነበረውን ሕግ (ሸሪዓ) እንዲያድስ ከአላህ፡ የሚታዘዝ ነቢይ ያልነበረው ሕዝብ የለም።

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ ولقد بعثنا فى كل أمة رسولا، ان اعبدوا الله، واجتنبوا الطاغوت﴾ النحل: ٣٦

﴿ وإن من أمة إلا خلا فيها نذير﴾ فاطر: ٢٤

57 አል- አሕዛብ /33/· 40

﴿إنا أنزلنا التوراة فيها هدى ونور، يحكم بها النبيون الذين أسلموا للذين هادوا﴾ المائدة:٤٤

« በየሕዝቡም ሁሉ ውስጥ፡ አላህን ተገዙ፡ ጣዖትንም ራቁ፡ በማለት መልክተኛን በእርግጥ ልከናል፡ ...»[58]

« ... ማንኛይቱም ሕዝብ በውስጧ አስፈራሪ ያላለፈባት የለችም።»[59]

« እኛ ተውራትን በውስጧ መምሪያና ብርሃን ያለባት ስትሆን አወረድናት፤ እነዚያ ትዕዛዝን የተቀበሉት ነቢያት በነዚያ ይሁዳውያን በኾኑት ላይ በርሷ ይፈርዱበታል ..»[60]

መልክተኞች (ሩሱል) ምንም ዓይነት የጌትነትም ሆነ የአምላክነት መለያ የሌላቸው ሰብዓዊ ፍጡራን ናቸው። የነቢያት ሁሉ ቁንጮና ከመልክተኞች ሁሉ አላህ ዘንድ ታላቅ ደረጃ ያላቸውን ነቢዩ ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) እንኳ አላህ (ሱ.ወ) ቁርአን ውስጥ እንዲህ ብሏቸዋል:-

﴿قل لا أملك لنفسى نفعا ولا ضرا إلا ماشاء الله، ولو كنت أعلم الغيب لاستكثرت من الخير وما مسني السوء، ان أنا الا نذير وبشير لقوم يؤمنون﴾ الأعراف:١٨٨

﴿قل انى لا أملك لكم ضرا ولا رشدا، قل انى لن يجيرنى من الله أحد، ولن أجد من دونه ملتحدا﴾ الجن:٢١ - ٢٢

« አላህ የሻውን በስተቀር ለራሴ ጥቅምንም ፡ ጉዳትንም፡ አልችልም፡ ሩቅንም (ምስጢር) የማውቅ በነበርኩ ኖሮ ከመልካም ነገር ባበዛሁ ክፉም ነገር ባልነካኝ

58 አል-ነሕል /16/: 36
59 ፋጢር /35/: 24
60 አል-ማኢዳህ /5/:44

ንገር፤ እኔ ለሚያምኑ ሕዝቦች አስፈራሪና አብሳሪ እንጂ ሌላ አይደለሁም በላቸው።»[61]

« እኔ ለናንተ ጉዳትንም ቀጥታንም አልችልም በላቸው። እኔ ከአላህ ቅጣት አንድም አያድነኝም፤ ከርሱም ሌላ መጠጊያን አላገኝም በላቸው።»[62]

መልክተኞች እንደሌላው ሰው ሁሉ የመታመም የሞት የመብላት የመጠጣትና ሌሎች ሁኔታዎች የሚታይባቸው ፍጡራን ናቸው። ለዚህ (ዐ.ሰ)ስለአላህ ኢብራሂም እንዲህ ብሏል:-

﴿والذى هو يطعمنى ويسقين، وإذا مرضت فهو يشفين، والذى يميتنى ثم يحيين﴾ الشعراء:٧٩ - ٨١

« ያም እርሱ የሚያበላኝና የሚያጠጣኝ ነው። በታመምኩ ጊዜ እርሱ ያሽረኛል። ያም የሚገድለኝ፤ ከዚያም ሕያው የሚያደርገኝ ነው።»[63]

ነቢዩ ሙሐመድም (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

(إنما أنا بشر مثلكم أنسى كما تنسون فإذا نسيت فذكرونى)

« እኔ እንደናንተው ሰው እንጂ ሌላ አይደለሁም። እናንተ እንደምትረሱ ሁሉ እኔም እረሳለሁና ስረሳ አስታውሱኝ።»

መልክተኞች አላህ ዘንድ ካላቸው ከፍተኛ ደረጃ ጋር ለአላህ ተገዢ ምቹና ትጉ ታዛዦች መሆናቸውን በማያሻማ ሁኔታ ተናግሯል። ነቢዩ ኢሳን (ዐ.ሰ) እና ነቢዩ ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) አስመልክቶ እንዲህ ብሏል:-

---

61 አል- አዕራፍ /7/:188
62 አል-ጂን/72/:21-22
63 አል-ሹዐራ /26/: 79-81

﴿ إنه كان عبدا شكورا﴾ الاسراء:٣

﴿ تبارك الذى نزل الفرقان على عبده ليكون للعالمين نذيرا﴾ الفرقان:١

«... እርሱ በጣም አመስጋኝ ባሪያ ነበርና።»[64]

« ያ ፉርቃንን (ሙትትን ከውሸት ለይውን መጽሐፍ ቁርአንን) በባሪያው ላይ፡ ለዓለማት አስፈራሪ ይሆን ዘንድ፡ ያወረደው (አላህ)፡ ክብርና ጥሬት ተገባው።»[65]

ስለ ነቢዮች አብረሃም፡ እስሐቅና ያዕቆብ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ واذكر عبادنـا إبراهيم، وإسحاق ويعقوب أولـي الأيـدي، والأبصار، إنا أخلصناهم بخالصة ذكرى الدار، وإنهم عندنا لمن المصطفين الأخيار﴾ ص:٤٥ - ٤٧

“ባሮቻችንን ኢብራሂምን፡ ኢስሐቅንና ያዕቆብንም፡ የኃይልና የማስተዋል ባለ ቤቶች የኾኑትን አውሳቸው። እኛ ጥሩ በኾነች ጠባይ መረጥናቸው፤ (እርሷም) የመጨረሻይቱን አገር ማስታወስ ናት። እነርሱም እኛ ዘንድ ከመልካሞቹ ምርጦች ናቸው።»[66]

ስለነቢዩ ዒሳም (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

---

64 አል-ኢስራእ /17/:3
65 አል- ፉርቃን/25/:1
66 ሷድ /38/: 45-47

﴿ان هو إلا عبد أنعمنا عليه وجعلناه مثلا لبنى اسرائيل﴾ الزخرف:٥٩

« እርሱ በርሱ ላይ የለገስንለት፡ ለእስራኤልም ልጆች ታምር ያደረግነው የኾነ ባሪያ እንጅ ሌላ አይደለም።»[67]

## በመልክተኞች (በሩሱል) ማመን አራት ነገሮችን ያካትታል

አንደኛ– ከአላህ በትክክል የተላኩ መሆናቸውን ማመን፤ ከመልክተኞች ውስጥ ያንዱንም መልክት ያስተባበለ ሰው በሁሉም የአላህ ነቢያትና መልክተኞች እንዳላመነ ይቆጠራል። አላህ (ሱ.ወ) ስለነቢዩ ኑሕ (ሰ.ዐ.ወ) ሕዝብ ሲናገር እንዲህ ብሏል:-

﴿كذبت قوم نوح المرسلين﴾ الشعراء:١٠٤

« የኑሕ ሕዝቦች መልክተኞችን አስተባበሉ።»[68]

የኑሕ ሕዝቦች በወቅቱ ያስተባበሉት መልክተኛውን ኑሕን ብቻ ቢሆንም አንዱን መልክተኛ ማስተባበል ማለት ከአላህ የተላኩ መልክተኞችን በጠቅሉ እንደማስተባበል ስለሚቆጠር አላህ (ሱ.ወ) ሕዝቦቹ ኑሕን ብቻ ሳይሆን ሁሉንም እንዳስተባበሉ ለማመልከት «መልክተኞችን አስተባበሉ» ብሏል። በዚህ መሠረትም ነቢዩ ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) ያስተባበሉና ያልተከተሏቸው ክርስትያኖች ሙሐመድን ብቻ ሳይሆን ነቢዩ ዒሳንም (ሰ.ዐ.ወ) ያስተባበሉና ያልተከተሏቸው ናቸው ማለት ነው። በተለይ ደግሞ ነቢዩ ዒሳ

67 አል- ዙኽሩፍ /43/: 59
68 አል- ሹዐራ /26/: 104

ዚሁ መሐመድ ከርሳቸው ዘመን በኋላ እንደሚመጡ ተከታዮቻቸውን አብስረው ነበር። ይህ ብስራት ከጥመት መንገድ የሚያድናቸውና ወደ ቀጥተኛው የአላህ ጎዳና የሚመራቸው የአላህ መልክተኛ ይመጣችኋል ከማለት ውጭ ሌላ ትርጉም ሊኖረው አይችልም።

ሁለተኛ– በስማቸው በተለይ ባወቅናቸው እንደ መሐመድ፣ ኢብራ ሂም ሙሳ፣ ዒሳና ኑሕ (ሰ.ዐ.ወ) ባሉት ማመን፤

እነዚህ አምስቱ « ኡሉል ዐዝም» ወይም ጽኑና ቆራጦቹ በመባል የሚታወቁ ሲሆን አላህ (ሱ.ወ) ቁርአን ውስጥ በተምሬት ሁለት ቦታ ላይ አውስቷቸዋል:-

﴿وإذ أخذنا من النبيين ميثاقهم ومنك ومن نوح، وإبراهيم، وموسى، وعيسى ابن مريم﴾ الأحزاب:٧

﴿شرع لكم من الدين ما وصى به نوحا والذى أوحينا إليك وما وصينا به إبراهيم، وموسى، وعيسى، أن أقيموا الدين ولاتتفرقوا فيه﴾ الشورى:١٣

« ከነቢያትም የጠበቀ ቃል ኪዳናቸውን፤ ካንተም፤ ከኑሕም፤ ከኢብራሂምም፤ ከሙሳም፤ ከመርየም ልጅ ዒሳም፤ በያዝን ጊዜ (አስታውስ)፤ ... »[69]

« ለናንተም ከሃይማኖት ያንን በርሱ ኑሕን ያዘዘበትን ደነገገላችሁ፤ ያንንም ወዳንተ ያወረድነውን፤ ያንንም በርሱ ኢብራሂምን፤ ሙሳንና ዒሳንም ያዘዝ ንበትን፤ ሃይማኖትን በትክክል አቋቁሙ፤ በርሱም አትለያዩ፤ ማለትን (ደነገገ)፤ ... »[70]

ስማቸውን የማናውቃቸውን ነቢያት በተመለከተ ግን በአጠቃላይ እናምንባቸዋለን። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

---

69 አል- አሕዛብ /33/: 7
70 አሽ- ሹራ /42/:13

﴿ولقد أرسلنا من قبلك منهم من قصصنا عليك ومنهم من لم نقصص عليك﴾ غافر:٧٨

«ካንተ በፊትም መልክተኞችን በእርግጥ ልከናል፤ ከነሱ ባንተ ላይ የተረክንልህ አለ፤ ከነሱም ባንተ ላይ ያልተረክነው አለ። ...»[71]

ሦስተኛ- ስለነሱ የተላለፈውንና ትክክለኛ የሆነውን ታሪክ አምኖ መቀበል፤ አራተኛ- ከነርሱ መካከል ወደኛ በተላኩት- በማጠቃለያቸው በሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ወደ መላው የሰው ልጅ የተላኩ መልክተኛ መሆናቸውን አምኖ በመቀበል ሕጋቸውን (ሸሪዓን) ተግባራዊ ማድረግ፤ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿فلا وربك لا يؤمنون حتى يحكموك فيما شجر بينهم، ثم لا يجدوا في أنفسهم حرجا مما قضيت ويسلموا تسليما﴾ النساء:٦٥

«በጌታህም እምላለሁ በመካከላቸው በተከራከሩበት ነገር እስኪያስፈርዱህ፤ ከዚያም ከፈረድከው ነገር በነፍሶቻቸው ውስጥ ጭንቀትን እስከማያገኙና ፍጹም መታዘዝን እስኪታዘዙ ድረስ አያምኑም፤ (ምእመን አይሆኑም)።»[72]

በመልክተኞች ማመን ከሚያስገኛቸው ጥቅሞች:-

አንደኛ- አላህ (ሱ.ወ) ለባሮቹ ምን ያህል ርህሩህ እንደሆነ ያሳውቃል። ወደ ቀጥተኛ ጎዳናው ሊመሩዋቸውና እርሱን እንዴት እንደሚገዙት ያብራሩላቸው ዘንድ አላህ (ሱ.ወ) ወደ ሰው ልጆች መልክተኞችን መላኩ

71 አል- ሙእሚን /40/: 78
72 አል- ኒሳእ /4/: 65

ለሰው ልጆች የለገሰውን ጸጋና እንክብካቤ ያመላክታል። የሰው ልጅ አእምሮ እነዚህን መለኮታዊ ሕግጋት በገዛ ራሱ ሊያውቅ አይችልምና።

ሁለተኛ– ለዚህ ታላቅ ጸጋ አላህን (ሱ.ወ) ማመስገን፤

ሦስተኛ– መልእክተኞችን መውደድ፡ ምክንያቱም፡ የአላህ (ሱ.ወ) መልእክተኞች ስለሆኑ፡ አላህን በፍጹምነት ስለሚገዙት የተጣለባቸውን ኃላፊነት ተወጥተው የአላህን መልእክት በታማኝነት ስላደረሱና ባሮቹን በቅንነት ስለመከሩ ተገዢያቸው በሆነ መንገድ መልእክተኞቹን ማወደስ፤

አላህ (ሱ.ወ) ከሰዎች መካከል መልእክተኞችን አይልክም፡ ሰብዓዊ ፍጡራን የአላህ መልእክተኛ መሆን አይችሉም በማለት ዕብሪተኞች መልእክተኞችን አስተባብለዋል። አላህ (ሱ.ወ) ይህን መሠረት የለሽ አባባል በማስተባበል እንዲህ ብሏል:-

﴿ وما منع الناس أن يؤمنوا إذ جاء هم الهدى إلا أن قالوا أبعث الله بشرا رسولا، قل لو كان فى الأرض ملائكة يمشون مطمئنين، لنزلنا عليهم من السماء ملكا رسولا﴾ الاسراء:٩٥

« ሰዎችንም፡ መሪ (ቁርአን) በመጣላቸው ጊዜ ከማመን፡ አላህ ሰውን መልእክተኛ አድርጎ ላከን? ማለታቸው እንጂ ሌላ አልከለከላቸውም። በምድር ላይ ረግተው የሚኼዱ መላእክት በነበሩ ኖሮ፡ በነሱ ላይ (በጎሳቸው) የመልአክን መልእክተኛ ባወረድን ነበር፡ በላቸው።»[73]

ከላይ እንደተመለከተው ሁሉ ሰዎች ወደሚኖሩበት መሬት የሚላክ መልእክተኛ እንደነሱው ያለ የሰው ልጅ ወገን መሆን አለበት፡ የምድር ነዋሪዎች መላእክት ቢሆኑ ኖሮ አላህ ከሰማይ መልአክን መልእክተኛ አድርጎ በላከላቸው ነበር በማለት አላህ (ሱ.ወ) አባባላቸውን ውድቅ አድርጓል።

---

73 አል– ኢስራእ /17/ 94-95

በተመሳሳይ ሁኔታም መልእክተኞችን ያስተማሀሉ ወገኖች የተናገሩትን እንደ ሚከተለው ገልጿል:-

﴿إن أنتم إلا بشر مثلنا تريدون أن تصدونا عما كان يعبد اباؤنا، فاتونا بسلطان بين، قالت لهم رسلهم: إن نحن إلا بشر مثلكم ولكن الله يمن على من يشاء من عباده، وما كان لنا أن نأتيكم بسلطان إلا بإذن الله﴾ إبراهيم: ١٠ ١١

« ... (ሕዝቦቹም) ፦ እናንተ ብጤያችን ሰው እንጂ ሌላ አይደላችሁም፤ አባቶቻችን ይግገዙት ከነበሩት ሊትከለክሉን ትሻላችሁ፤ ግልጽንም አስረጅ (ከመጣችሁት ሌላ) አምጡልን አሉ። መልክተኞቻቸውም ለነርሱ አሉ:- እኛ ብጤያችሁ ሰው እንጂ ሌላ አይደለንም፤ ግን አላህ ከባሮቹ በሚሻው ሰው ላይ ይለግሳል፤ ለኛም በአላህ ፈቃድ እንጂ ማስረጃን ልናመጣላችሁ አይገባንም፤...»[74]

74 ኢብራሂም /14/: 10-11

## በመጨረሻው ቀን ማመን

የመጨረሻው ቀን ማለት ሰዎች ከሞት ተቀስቅሰው ለምርመራና እንደየሥራቸው ተገቢ ምንዳቸውን ለመቀበል የሚነሱበት የትንሣኤ ቀን ነው። የመጨረሻ ቀን የተባለበት ምክንያት ገነት የሚገቡትም ሆኑ ገሀነም የሚገቡት ሁሉም በየቤቱ ስለሚገባ ከዚያ ቀን በኋላ ሌላ ቀን ስለሌለ ነው።

## በመጨረሻው ቀን ማመን ሦስት ነገሮችን ያጠቃልላል

<u>አንደኛ</u>- ከሞቱ በኋላ ዳግም መቀስቀስ (በዕስ) መኖሩን ማመን፤ ይህ ማለት ሁለተኛው መለከት ሲነፋ ሙታን በሙሉ ራቁታቸውን ያለምንም ልብስ፣ ያለ ጫማ ባዶ እግራቸውን ያልተገረዙ ሆነው የዓለማት ፈጣሪ ጌታ ፊት ለፍርድ ለመቅረብ በሚቀሰቀሱበት ቀን ማመን ማለት ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፦

﴿كما بدأنا أول خلق نعيده وعدا علينا إنا كنا فاعلين﴾

الأنبياء: ١٠٤

« ... የመጀመሪያን ፍጥረት እንደ ጀመርን፣ እንመልሰዋለን፤ (መፈጸም) በኛ ላይ የሆነን ቀጠሮ ቀጠርን፤ (የተጠረነውን) ሠሪዎች ነንም።»[75]

ከሞት መቀስቀስ ቁርኣን ሱንና እና የሙስሊሞች የጋራ አቋም (እጅማዕ) ያረጋገጡት ፍጹ ግዴ እውነት ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ثم إنكم بعد ذلك لميتون، ثم إنكم يوم القيامة تبعثون﴾ المؤمنون: ١٥ - ١٦

«ከዚያም እናንተ ከዚህ በኋላ በእርግጥ ሟቾች ናችሁ። ከዚያም እናንተ በትንሣኤ ቀን ትቀሰቀሳላችሁ።» [76]

ነቢዩም (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

(يحشر الناس يوم القيامة حفاة غرلا) متفق عليه

« ሰዎች በትንሣኤ ቀን ባዶ እግራቸውን ያልተገረዙ ሆነው ከሞት ይቀሰቀሳሉ።»[77]

---

75 አል- አንቢያ /21/: 104
76 አል- ሙእሚኑን /23/: 15-16
77 ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት ሐዲስ

የሙስሊሞች የጋራ አቋምም ይህንኑ ያረጋግጣል። ይህ ፍጥረት መጨረሻ ኖሮት ሁሉም ነገ ከጠፋ በኋላ ሰዎች ሁሉ የየሥራቸውን ዋጋ ቀደም ሲል አላህ በላካቸው ነቢያት አማካይነት የተላለፈላቸውን መለኮታዊ ሕግ በመተግበር ረገድ ባደረጉት ጥረት ላይ የተመረኮዘ ምንዳ ወይም ቅጣት የግዴታ ማግኘት እንዳለባቸው የአላህ (ሱ.ወ) ጥበብ የሚወስነው ጉዳይ ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ افحسبتم انما خلقناكم عبثاء وأنكم إلينا لاترجعون﴾

المومنون:١١٥

« የፈጠርናችሁ፣ ለከንቱ መኾኑን እናንተም ወደኛ የማትመለሱ መኾናችሁን ጠረጠራችሁን?»[78]

አላህ (ሱ.ወ) ለነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ إن الذى فرض عليك للقرآن لرادك الى معاد﴾

القصص:٨٥

« ያ ቁርአንን የተከፋፈለ ቾና ባንተ ላይ ያወረደው (አምላክ)፣ ወደ መመለሻ በእርግጥ መላሽህ ነው፣ ...»[79]

<u>ሁለተኛ</u> – ምርመራ መኖሩንና ለሁሉም እንደየሥራው ዋጋ የሚሰጠው መሆኑን ማመን፤ አንድ ሰው በመጀመሪያ ምድራዊ ሕይወቱ በፈጸማቸው ሥራዎች ሁሉ ላይ ምርመራ ይደረግበትና መልካም ሠርቶ ከሆነ ገነት መጥፎ ሠርቶ ከሆነም የከፋ የገሐነም እሳት ይገባል። ይህ እምነት በቁርአን በሱና– እና በሙስሊሞች የጋራ አቋም (ኢጅማዕ) የተረጋገጠ ነው።

አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

---

78 አል– ሙእሚኑን /23/: 115
79 አል–ቀሶስ /28/: 85 .

﴿ان الينا ايابهم ثم إن علينا حسابهم﴾ الغاشية: ٢٥ ٢٦

﴿من جاء بالحسنة فله عشر امثالها، ومن جاء بالسيئة فلا يجزى إلا مثلها، وهم لايظلمون﴾ الأنعام: ١٦٠

﴿ونضع موازين القسط ليوم القيامة، فلاتظلم نفس شيئا، وان كان مثقال حبة من خردل أتينا بها، وكفى بنا حاسبين﴾ الأنبياء: ٤٧

«መመለሻቸው ወደኛ ብቻ ነው። ከዚያም ምርመራቸው በኛ ላይ ብቻ ነው።»[80]

«በመልካም ሥራ የመጣ ሰው፡ ለርሱ ዐሥር ብጤዎችዋ አሉት፤ በክፉ ሥራም የመጣ ሰው ብጤዋን እንጅ አይመነዳም፤ እነርሱም አይበደሉም።»[81]

«በትንሣኤም ቀን ትክክለኛ ሚዛኖችን እናቆማለን፡ ማንኛይቱም ነፍስ ምንንም አትበደልም፤ (ሥራው) የሰናፍጭ ቅንጣት ያክል ቢኾንም እርሷን እናመጣታለን፤ ተቆጣጣሪዎችም በኛ በቃ።»[82]

ከአብነት ዑመር በተላለፈው ሐዲስ ውስጥ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

( ان الله يدني المؤمن فيضع عليه كنفه ويستره، فيقول: أتعرف ذنب كذا؟ أتعرف ذنب كذا؟ فيقول نعم: أى رب حتى إذا قرره بذنوبه، ورأى أنه قد هلك قال: قد سترتها

80 አል- ጋሺያህ /88/: 25-26
81 አል- አንዓም /6/· 160
82 አል- አንቢያ /21/. 47

عليك فى الدنيا، ولنا أغفرها لك اليوم، فيعطى كتاب حسنلته، ولما الكفار والمنافقون فينادى بهم على رؤس الخلائق (هؤلاء الذين كذبوا على ربهم، ألا لعنة الله على الظالمين) متفق عليه

(إن من هم بحسنة فعملها، كتبها الله عنده عشر حسنات إلى سبعمائة ضعف إلى أضعاف كثيرة، ولن من هم بسيئة فعملها، كتبها الله سيئة واحدة)

« አላህ አማኝ የሆነ ሰውን (ሙእምንን) ያቀርብና ከሰዎች በመሸፈን:- ‹እንዲህ ያለውን ኃጢአትህን እንደዚህ ያለውን ኃጢአትህን ታውቃለህ?› ይለዋል። (አማኙም) አዎ ጌታዬ አውቃለሁ ይላል። ኃጢአቶቹን አሳምኖት ጥፋት እንደተረጋገጠበት የተረዳ መሆኑን ሲመለከትም:- ‹በመጀመሪያ ምድራዊ ሕይወትህ ጊዜም ደብቄልሃለሁ፤ እኔም ዛሬም ይቅር ብዬ እምርሃለሁ› ይለውና አማኙ የመልካም ሥራዎቹን መዝገብ ይሰጠዋል። ለከሓዲዎችና፡ለአስመሳይ መናፍቃን ግን ‹እነዚህ ጌታቸው ላይ የቀጠፉ ናቸው፤ የአላህ ቁጣም በበዳዮች ላይ ይሁን› ተብሎ በተሰበሰቡ ፍጡራን ፊት ይታወጃል።»[83]

« አንድ ሰው መልካም ሥራ ለመሥራት አስቦ ከሠራው አላህ ከእርሱ መልካም ምንዳ ጀምር እስከ ሰባት መቶ እጥፍና እስከ ብዙ እጥፍ ድርብ ምንዳ ድረስ እርሱ ዘንድ ይጽፍለታል። አንድ ሰው መጥፎ ነገር አስቦ ከሠራው ግን አንድ መጥፎ ሥራ ብቻ አላህ ይመዘግብበታል።»

ምርመራ ስለመኖሩና ለሁሉም እንደ የሥራው ተገቢ ዋጋ የሚከፈለው ስለመሆኑ መስሊሞች በአንድ ድምጽ የተስማሙበት እውነታ ነው። የአላህ (ሱ.ወ) ጥበብም ይህንኑ ግዴታ ያደርጋል። አላህ (ሱ.ወ) መጽሕፍት አውርዷል። መልክተኞችን ልኳል። መልክተኞች ያስተማሩትን ነገር እንዲቀበሉና ተግባራዊ እንዲያደርጉ በሰዎች ላይ ግዴታ ጥሏል። መልክተኞቹ ያስተማሩትን የሚጻረሩ ወገኖችን መዋጋት ልጆቻቸውን ሴቶቻቸውንና ንብረታቸውን መውረስ ፈቅዷል። ምርመራ ጥያቄና ለሁሉም እንደ የሥ-

83 ቡኻሪና ሙስሊም የዘገቡት ሐዲስ

ራው ምንዳ ወይም ቅጣት የመስጠት ፍትሕ የሚያኖር ቢሆን ኖር ይህን ሁሉ መደንገግ ከንቱ በሆነ ነበር። ሦስተኛው አምላክ፣ አላህ (ሱ.ወ) ከዚህ ከንቱነት የጠራ ጌታ ነው። ይህን እውነታ አስመልክቶ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ فلنسألن الذين أرسل إليهم، ولنسألن المرسلين،فلنقصن
عليهم بعلم،وما كنا غائبين﴾

الأعراف: ٦ – ٧

«እነዚያንም ወደነሱ ነብያት የተላከባቸውን (ሕዝቦች) በእርግጥ እንጠይቃቸዋለን። የተላኩትን መልዕክተኞችንም በእርግጥ እንጠይቃለን፤ በነርሱም ላይ (የነበሩበትን ሁሉ) ከዕውቀት ጋር በእርግጥ እንተርክላቸዋለን፤ የራቅንም አልነበርንም።» [84]

ሦስተኛ– ገነትና እሳት (ገሐነም) መኖሩን ማመን፤

በገነትና በእሳት (ገሐነም) መኖር ማመን ማለት የፍጥረታት ሁሉ መጨረሻ ከሁለቱ በአንደኛው መሆኑን ማመን ማለት ነው። ጀነት የነዚያ አላህ እንዲያምኑ በጠየቃቸው ነገር ሁሉ ያመኑ አላህንና መልክተኛውን በቅንነት የታዘዙ ለአላህ ፍጹም በመሆን መልክተኞቹን ለተከተሉ ፈሪሀ አላህ የሆኑ ምዕመናን አገር ነች። ገነት ታይተውና ተሰምተው የማይታወቁ፣ በሰው አእምሮ ታስበው የማይታወቁ የመደሰቻ ዓይነቶች የተትረፈረፉባት መኖሪያ አገር ነች። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ إن الذين ءامنوا وعملوا الصالحات، أولئك هم خير البرية،
جزاؤهم عند ربهم جنات عدن تجرى من تحتها الأنهار، خالدين
فيها أبدا، رضي الله عنهم ورضوا عنه، ذلك لمن خشي ربه﴾

البينة: ٧ – ٨

---

84 አል- አዕራፍ /7/: 6-7

﴿ فلا تعلم نفس ما أخفي لهم من قرة أعين جزاء بما كانوا يعملون﴾ السجدة:١٧

« እነዚያ ያመኑትና መልካሞችንም የሠሩት፥ እነዚያ እነሱ ከፍጥረት ሁሉ በላጮ ናቸው። በጌታቸው ዘንድ ምንዳቸው ከሥሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸው የመኖሪያ ገነቶች ነው፤ በውስጣቸው ለዘላለም ዘውታሪዎች ሲኾኑ፥ (ይገቡባቸዋል)። አላህ ከነሱ ወደደ ፤ ከርሱም ወደዱ፤ ይህ ጌታውን ለፈራ ሰው ነው።»[85]

« ይሠሩትም በነበሩት ለመመንዳት፥ ከዓይኖች መርጊያ ለነሱ የተደበቀላቸውን (ጸጋ)፡ ማንኛይቱም ነፍስ አታውቅም።»[86]

እሳት (ገሐነም) ደግሞ እርሱን ባስተባበሉና መልክተኞቹ ላይ ባመጹ ከሐዲዎችና በዳዮች አላህ (ሱ.ወ) ያዘጋጀላቸው የሥቃይ ሥፍራ ነች። ይህ ነው ተብሎ የማይታሰብ የሥቃይና የውርደት ዓይነቶች ያጠቃለለች የመቀ ማጫ ቦታ ነች። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ واتقوا النار التي أعدت للكافرين﴾ آل عمران:١٣١

﴿ إنا أعتدنا للكافرين نارا أحاط بهم سرادقها، وان يستغيثوا يغاثوا بماء كالمهل يشوى الوجوه، بئس الشراب وساءت مرتفقا﴾ الكهف:٢٩

﴿ إن الله لعن الكافرين، وأعد لهم سعيرا، خالدين فيها أبدا، لا يجدون وليا ولا نصيرا، يوم تقلب وجوههم فى النار، يقولون يا ليتنا أطعنا الله وأطعنا الرسولا﴾ الأحزاب، ٦٤ - ٦٦

85 አል- በይናህ /98/:7-8
86 አል- ሰጅዳህ /32/: 17

« ያችንም ለከሐዲዎች የተደገሰችውን እሳት ተጠንቀቁ፡፡ »[87]

« ... እኛ ለበደለኞች አጥርዋ በነሱ የከበበ የሆነችውን እሳት አዘጋጅተናል፡ (ከጥም) እርዳታንም ቢፈልጉ፡ እንደዘይት ዝቃጭ ባለ ፊቶችን በሚጠብስ ውሃ፡ ይረዳሉ፡ መጠጡ ከፋ! መደገፊያይቱም ምንኛ አስከፋች! »[88]

« አላህ ከሐዲዎችን በእርግጥ ረግሟቸዋል፡ ለነርሱም የተጋጋመችን እሳት አዘጋጅቷል። በርሷ ውስጥ ዘለዓለም ዘውታሪዎች ሲኾኑ፡ ወዳጅም ረዳትም አያገኙም። ፊቶቻቸው በእሳት ውስጥ በሚገለባበጡ ቀን፡ ዋ ምኞታችን! አላህን በተገዛን፡ መልክተኛውንም በታዘዝን ኖሮ እያሉ ይጸጸታሉ፡፡ »[89]

ከሞት በኋላ በሚሆን መቃብር ውስጥ በሚኖረው ሥቃይ ፈተናና ደስታ በመሳሰሉት ነገሮች ማመን በመጨረሻው ቀን በማመን ሥር ይጠቃለላል።

ሀ- የመቃብር ውስጥ ፈተና፡- ይህ ፈተና ሟቹ ከተቀበረ በኋላ ጌታው ማን እንደሆነ፡ ሃይማኖቱ ምን እንደሆነና ነቢዩ ማን እንደሆነ የሚጠየቅበት ፈተና ነው። በዚህ ፈተና ወቅት በጽኑው የአላህ ቃል ላመኑ ምዕመናን አላህ (ሱ.ወ) ጽናት ይሰጥና– ጌታዩ አላህ ነው፡ ሃይማኖቴ እስላም ነው፡ ነቢዩም ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ናቸው በማለት ይመልሳሉ። አላህ በዳዮችን ያጠምና ከሐዲዎች ሃ! ሃ! አላውቅም ብለው ይመልሳሉ። እስመላይ መናፈቁ ወይም ተጠራጣሪው ደግሞ፡ አላውቅም ሰዎች ሲሉ ሰምቼ ነው ያልኩት ብሎ ይመልሳል።

ለ- መቃብር ውስጥ ያለው ሥቃይና ደስታ፡- የመቃብር ውስጥ ሥቃይን በተመለከተ በዳዮች መናፍቃንና ከሐዲዎች መቃብራቸው ውስጥ ይሠቃያሉ። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል፡-

---

87 አል-ዒምራን /3/: 131
88 አል-ከሃፍ /18/: 29
89 አል- አሕዛብ /33/: 64–66

﴿ولو ترى إذ الظالمون في غمرات الموت، والملائكة باسطوا أيديهم، أخرجوا أنفسكم، اليوم تجزون عذاب الهون بما كنتم تقولون على الله غير الحق وكنتم عن آياته تستكبرون﴾

الأنعام:٩٣

« ... በደለኞችንም በሞት መከራዎች ውስጥ በሆኑ ጊዜ መላእክት እጆቻቸውን ዘርጊዎች ኾነው (ለቅጣት) ነፍሶቻችሁን አውጡ! በአላህ ላይ እውነት ያልኾነን ነገር ትናገሩ በነበራችሁትና ከአንቀጾቹም ትኮሩ በነበራችሁት ምክንያት፡ ዛሬ የውርደትን ቅጣት ትመነዳላችሁ፡ (የሚሉዋቸው ሲኾኑ) ብታይ ኖሮ፡( አስደናቂን ነገር ባየህ ነበር)።»[90]

﴿النار يعرضون عليها غدوا وعشيا، ويوم تقوم الساعة أدخلوا آل فرعون أشد العذاب﴾ غافر:٤٦

« እሳት በጧትና በማታ በርሷ ላይ ይቀረባሉ፤ ሰዓቲቱም በምትቆምበት ቀን የፈርዖንን ሰዎች ብርቱን ቅጣት (ገሀነምን) አግቡዋቸው (ይባላል)።»[91]

ሙስሊም ዘይድ ብን ሳቢትን በመጥቀስ በዘገቡት ሐዲስ ውስጥ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

( فلولا أن لا تدافنوا لدعوت الله أن يسمعكم من عذاب القبر الذي أسمع منه، ثم أقبل بوجهه فقال: تعوذوا بالله من عذاب النار قالوا: نعوذ بالله من عذاب النار. فقال: تعوذوا من عذاب القبر، قالوا: نعوذ بالله من عذاب القبر، قال: تعوذوا من الفتن ما

90 አል- አንዓም /6/: 93
91 አል- ሙእሚን /40/: 46

ظهر منها وما بطن، قالوا: نعوذ بالله من الفتن ما ظهر منها وما بطن، قال: تعوذوا بالله من فتنة الدجال قالوا: نعوذ بالله من فتنة الدجال) رواه مسلم

«... (ደምሩን በመስጊታችሁ ምክንያት ሬሳችሁን) መቃብር ትተዋላችሁ በዚ-ሻለሁ ኖር እኔ እየሰማሁ ያለሁትን (የመቃብሩ ስቃይ ያለበትን) የመቃብር ሥቃይ አላህ እንዲያሰማችሁ በለመንኩ ነበር።» አለና ፊታቸውን ወደ ሰሓቦች በማዞር:- ‹ከእሳት ቅጣት በአላህ ተጠበቁን በሉ› አሏቸው። እነሱም አላህ ሆይ! ከእሳት ቅጣት በአንተ እንጠበቃለን አሉ። ‹ከመቃብር ቅጣት በአላህ ተጠበቁ› አሏቸው። ከመቃብር ቅጣት በአላህ እንጠበቃለን አሉ። ‹ከፊተናዎች ከግልጹም ከስውሩም በአላህ ተጠበቁን በሉ› አሏቸው። ከፊተናዎች ከግልጹም ከስውሩም በአላህ እንጠበቃለን አሉ። ‹ከደጃ-ጃል ፊተና በአላህ ተጠበቁን በሉ› አሏቸው። ከደጃ-ጃል ፊተና በአላህ እንጠበቃለን አሉ።»[92]

፩.፬

የመቃብር ውስጥ ደስታ ግን ለእውነተኞቹ ምዕመናን ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ إن الذين قالوا ربنا الله تتنزل عليهم الملائكة أن لا تخافوا ولاتحزنوا، وأبشروا بالجنة التى كنتم توعدون﴾
فصلت: ٣٠

﴿ فلولا إذا بلغت الحلقوم، وأنتم حينئذ تنظرون، ونحن أقرب إليه منكم ولكن لاتبصرون، فلولا ان كنتم غير مدينين، ترجعونها ان كنتم صادقين، فأما إن كان من المقربين فروح وريحان وجنة نعيم..﴾ الواقعة:٨٣ – ٨٩٠

92 ሙስሊም የዘገበው ሐዲስ

« እንዚያ ጌታችን አላህ ነው ያሉ፡ ከዚያም ቀጥ ያሉ፤ አትፍሩ፤ አትዘኑም፤ በዚያችም ተስፋ ቃል ትደረግላችሁ በነበራችሁት ገነት ተበሰሩ፡ በማለት በነሱ ላይ መላእክት ይወርዳሉ።»[93]

« (ነፍስ) ጉሮሮንም በደረሰች ጊዜ እናንተ ያን ጊዜ የምታዩ ስትኾኑ። እኛም፡ ግን አታዩም እንጅ ከናንተ ይልቅ ወደርሱ የቀረብን ስንኾን። የማትዳኙም ከኾናችሁ። እውነተኞች እንደኾናችሁ፡ (ነፍሲቱን ወደ አካሉ) ለምን አትመልሷትም። (ሟቹ) ከባለሟሎቹ ቢኾንማ። (ለርሱ) ዕረፍት፡ መልካም ሲሳይም፡ የመጠቀሚያ ገነትም አለለው።»[94]

አንድ አማኝ (ሙእሚን) ለሁለቱ መላእኮች ጥያቄ መልስ ሲሰጥ የሚሆነውን ሁኔታ አስመልክተው ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል፡-

( ينادى مناد من السماء أن صدق عبدي، فافرشوه من الجنة، والبسوه من الجنة، وافتحوا له بابا إلى الجنة، قال فيأتيه من روحها وطيبها، ويفسح له فى قبره مد بصره) رواه أحمد

« ከሰማይ ጠሪ ይጣራና ባሪያዬ እውነት ተናገረና ከገነት (ምንጣፍ) አንጥፉለት፡ ከገነት (ልብስ) አልብሱት፡ ወደ ገነት የሚወስድ በርም ክፈቱለት ይላል። በዚህም (ከገነት) አርይታዋና መልካም መዓዛ ይመጡለታል፡ የዓይኑ እይታ እስከ ሚደርስበት ርቀት ድረስም መቃብሩ ይሰፋለታል።»[95]

በመጨረሻው ቀን ማመን ከሚያስገኛቸው ከፍተኛ ውጤቶች መካከል፡-

<u>አንደኛ</u>:- ለዚያ ቀን ምንዳ ተስፋ በማድረግ ለመልካም ሥራ መጓጓትና ፍላጎት ማሳደግ፤

93 ፉሲለት አለበጅላሁ /41/:30
94 አል- ዋቂዓህ /56/: 83-89
95 አሕመድ የዘገቡት ሐዲስ

ሁለተኛ:- የአላህን ትዕዛዝ መጣስ በዚያ ቀን የሚያስከትለውን መራር ቅጣት በማሰብ ከክፉ ሥራ የመቆጠብ ገፊት ማሳደጉ፣

ሦስተኛ:- አንድ አማኝ (ሙእሚን) በዚህች ጠፊ ዓለም ከሚያመልጡት ነገሮች በወዲያኛው ዓለም በሚኖረው ተድላና ምንዳ መጽናናቱ፣ ይገኙበታል።

ከሓዲዎች ከሞት በኋላ ዳግም መቀስቀስ የማይቻል ነው በማለት አስተባብለዋል። ይህ አባባል ግን ሸሪዓው ተጨባጩ ሁኔታና አእምሮ በማስረጃ የሚያስተባብሉት ውሸት ነው።

የሸሪዓን ማስረጃ በተመለከተ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿زعم الذين كفروا ان لن يبعثوا قل بلى وربى لتبعثن، ثم لتنبؤن بما عملتم، وذلك على الله يسير﴾ التغابن:٧

«እነዚያ የካዱት በፍጹም የማይቀሰቀሱ መኾናቸውን አሰቡ፤ አይደለም በጌታዬ እምላለሁ፤ በእርግጥ ትቀሰቀሳላችሁ፤ ከዚያም በሠራችሁት ሁሉ ትነገራላችሁ፤ ይህም በአላህ ላይ ቀላል ነው፤ በላቸው።»[86]

መለኮታዊ መጻሕፍትም በዚህ ነጥብ ላይ ሙሉ በሙሉ ይስማማሉ። ተጨባጭ ሁኔታን በተመለከተ ደግሞ አላህ (ሱ.ወ) በዚህች ዓለም ላይ ሰዎች ከሞቱ በኋላ ከመቃብራቸው ነፍስ ዘርተው እንዲቀሰቀሱ በማድረግ አሳይቷል። በአል-በቀራህ ምዕራፍ ውስጥ ይህንኑ የሚያረጋግጡ አምስት ምሳሌዎች ተመልክተዋል።

አንደኛው ምሳሌ:- የነቢዩ ሙሳ (ሰ.ዐ.ወ) ሕዝቦች አላህን በዓይናችን ካላየን በስተቀር አናምን ባሉ ጊዜ አላህ (ሱ.ወ) ገድሏቸው እንደገና አስነስቷቸዋል።

---

86 አል- ተጋቡን /64/: 7

ይህንኑ በማስመልከት አላህ (ሱ.ወ) ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ብሏል:-

﴿وإذ قلتم يا موسى لن نؤمن لك حتى نرى الله جهرة، فأخذتكم الصاعقة، وأنتم تنظرون، ثم بعثناكم من بعد موتكم لعلكم تشكرون﴾ البقرة: ٥٤ - ٥٦

« ሙሳ ሆይ! አላህን በግልጽ እስከምናይ ድረስ ላንተ በፍጹም አናምንልህም ባላችሁም ጊዜ (አስታውሱ)፤ እናንተም እየተመለከታችሁ መብረቅ ያዘቻችሁ፤ (ሰባዎቹ ምርጦቻችሁ ሞቱ)። ከዚያም ታመሰግኑ ዘንድ ከሞታችሁ በኋላ አስነሳናችሁ።»[97]

<u>ሁለተኛው ምሳሌ</u>:- የእስራኤል ልጆች ከመካከላቸው ገዳዩ ባይታወቅ ሞቶ የተገኘውን ሰው ታሪክ የሚመለከት ሲሆን የሟችን ገዳይ ለማወቅ አላህ ባዘዛቸው መሠረት ላም አርደው በላሟ ከፊል አካል ሟችን ሲመቱ ሟች ሕይወት ዘርቶ ገዳዩ ማን እንደሆነ ተናገረ። ይህን አስመልክቶ አላህ (ሱ.ወ) ቁርአን ውስጥ እንዲህ ብሏል:-

﴿وإذ قتلتم نفساً فادارأتم فيها، والله مخرج ما كنتم تكتمون، فقلنا اضربوه ببعضها كذلك يحيي الله الموتى، ويريكم آياته لعلكم تعقلون﴾ البقرة: ٧٢ - ٧٣

« ነፍስንም በገደላችሁና በርሷም (ገዳይ) በተከራከራችሁ ጊዜ (አስታውሱ)፤ አላህም ትደብቁት የነበራችሁትን ሁሉ ገላጭ ነው። (ሬሳን) በከፊሏ (በላሚቱ ቁራጭ) ምቱት አልን፤ (መታችሁትም ተነሳ ገዳዩንም ተናገረና ሞተ)፤ እንደዚሁ አላህ ሙታንን ያስነሳል፤ ታውቁም ዘንድ ታምራቶቹን ያሳያችኋል።»[98]

97 አል-በቀራህ /2/: 54-56
98 አል-በቀራህ /2/: 72-73

ሦስተኛው ምሳሌ:- ሞትን ለመሸሽ በሺዎች የሚቆጠሩ ሆነው ከአገራቸው የወጡትን ሰዎች ታሪክ የተመለከተ ሲሆን እነዚህን ሰዎች አላህ ከገደላቸው በኋላ እንደገና ቀስቅሷቸዋል። ይህንኑ በማስመልከት አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ألم ترى إلى الذين خرجوا من ديارهم وهم ألوف حذر الموت، فقال لهم الله موتوا، ثم أحياهم إن الله لذو فضل على الناس، ولكن أكثر الناس لا يشكرون﴾
البقرة:٢٤٣

« ወደ እነዚያ እነርሱ ብዙ ሺሕ ኾነው ሞትን ለመፍራት ከሀገሮቻቸው ወደ ወጡት ሰዎች አልተመለከትህምን? አላህም ለነርሱ ሙቱ አላቸው፤ (ሞቱም)፤ ከዚያም ሕያው አደረጋቸው፤ አላህም በሰዎች ላይ ባለችሮታ ነው፤ ግን አብዛኞቹ ሰዎች አያመሰግኑም።»[90]

አራተኛው ምሳሌ:- በአንዲት የወደመች ከተማ ውስጥ ሲያልፍ ይህች የጠፋች ከተማ እንዴት ዳግም መቀስቀስ ትችላለች ብሎ በመገረም የተናገረውን ሰው ታሪክ የሚመለከት ነው። አላህ (ሱ.ወ) ይህን ሰው አንድ መቶ ዓመት ሞቶ እንዲቆይ ካደረገው በኋላ እንደገና የቀሰቀሰው መሆኑን እንደሚከተለው ተናግሯል:-

﴿أو كالذي مر على قرية وهي خاوية على عروشها قال: أنى يحيي هذه الله بعد موتها، فأماته الله مئة عام، ثم بعثه، قال: كم لبثت؟ قال: لبثت يوما أو بعض يوم؛

90 አል-በቀራህ /2/: 243

قال: بل لبثت مئة عام فانظر إلى طعامك وشرابك لم يتسنه وانظر إلى حمارك ولنجعلك آية للناس وانظر إلى العظام، كيف ننشزها، ثم نكسوها لحما؟ فلما تبين له قال: اعلم أن الله على كل شيئ قدير﴾ البقرة:٢٥٩

«ወይም ያንን በከተማ ላይ እርሷ በጣራዎችዋ ላይ የወደቀች ስትኾን ያለፈውን ሰው ብጤ፤ (አላየህምን?):- ይህችን (ከተማ) ከሞተች በኋላ አላህ እንዴት ሕያው ያደርጋታል? አለ፤ አላህም ገደለው፤ መቶ ዓመትን (አቆየውም)፤ ከዚያም አስነሳው:- ምን ያህል ቆየህ? አለው፤ አንድን ቀን ወይም የቀንን ከፊል ቆየሁ አለ፤ አይደለም መቶን ዓመት ቆየህ፤ ወደ ምግብህና ወደ መጠጥህም ያልተለወጠ ሲኾን፤ ተመልከት፤ ወደ አህያህም ተመልከት፤ ለሰዎችም አስረጅ እናደርግህ ዘንድ፤ (ይህን ሠራን)፤ ወደ ዐጥንቶችም እንዴት እንደምናስነሳት ከዚያም ሥጋን እንደምናለብሳት ተመልከት፤ አለው፤ ለርሱም (በግልጽ) በተገለጸ ጊዜ:- አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ መኾኑን ዐውቃለሁ፤ አለ።»[100]

<u>አምስተኛው ምሳሌ</u>:- ተወዳጁ ነቢዩ ኢብራሂም (ሰ.ዐ.ወ)፤ አላህ (ሱ.ወ) ሙታንን እንዴት እንደገና እንደሚያስነሳ እንዲያሳያቸው የለመኑበትን ሁኔታ የሚመለከት ታሪክ ነው። በዚህ መሠረትም አላህ (ሱ.ወ) አራት ወፎችን አርደው በመበለት በአካባቢያቸው በነበሩት ተራሮች ላይ የወፎቹን ሥጋ እንዲያስቀምጡ ኢብራሂምን አዘዛቸው። ኢብራሂም የታዘዙትን ከፈጸሙ በኋላ ወፎቹን ሲጣሩ በተራሮች ላይ የተበታተኑ አካሎቻቸው እየተገጣጠሙ ወደ ኢብራሂም እየሮጡ መጡ።

ይህንኑ አስመልክቶ አላህ (ሱ.ወ) ቁርአን ውስጥ እንዲህ ብሏል:-

﴿وإذ قال إبراهيم رب أرني كيف تحيي الموتى؟ قال: أولم تؤمن! قال: بلى، ولكن ليطمئن قلبي. قال: فخذ

100 አል-በቀራህ/2/: 259

أربعة من الطير فصرهن إليك، ثم اجعل على كل جبل منهن جزءا ثم ادعهن يأتينك سعيا، واعلم ان الله عزيز حكيم﴾ البقرة: ٢٦٠

« ኢብራሂም ጌታዬ ሆይ! ሙታንን እንዴት ሕያው እንደምታደርግ አሳየኝ ባለ ጊዜ፣ (አለስታውስ፣ አላህ):- አላመንክምን? አለው፤ አይደለም (አምኛለሁ)፤ ግን ልቤ እንዲረጋ ነው አለ፣ (አላህም):- ከበራሪዎች (ከወፎች) አራትን ያዝ፣ ወደ አንተም ሰብስባቸው፤ (ቆራርጣቸውም)፤ ከዚያም በኮረብታው ሁሉ ላይ ከነርሱ ቁራጭን አድርግ፤ ከዚያም ጥራቸው፤ ፈጥነው ይመጡሃልና፤ አላህም አሸናፊ ጥበበኛ መኾኑን ዕወቅ አለው።» [101]

እነዚህ ሙታንን እንደገና ወደ ሕይወት መመለስ የሚቻል መሆኑን በተጨባጭ የሚያሳዩ ምሳሌዎች ናቸው። ቀደም ሲል ለመርየም ልጅ ለዒሳ ሙታንን በአላህ (ሱ.ወ) ፈቃድ ከመቃብር በማስነሳት የሰጠውን ተአምራት አውስተናል።

## ሕሊናዊ ማስረጃው ደግሞ በሁለት ይከፈላል

አንደኛ:- አላህ (ሱ.ወ) ሰማያትንና መሬትን በውስጣቸው ያሉትን ፍጥረታት በአጠቃላይ ከመጀመሪያው የፈጠረ አምላክ ነው። ፍጥረታትን መጀመሪያ ማስገኘት የቻለ ፈጣሪ እንደገና ከጠፉ በኋላ መልሶ ማስገኘት አይሳነውም። ይህንኑ በማስመልከት አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿وهو الذى يبدأ الخلق ثم يعيده، وهو أهون عليه﴾

الروم: ٢٧

---

101 አል- በቀራህ /2/: 260

﴿كما بدأنا أول خلق نعيده، وعدا علينا، إنا كنا فاعلين﴾ الأنبياء:١٠٤

« እርሱም፣ ያ መፍጠርን የሚጀምር፣ ከዚያም የሚመልሰው ነው፣ እርሱም (መመለሱ) በእርሱ ላይ በጣም ገር ነው ...»[102]

« ... የመጀመሪያን ፍጥረት እንደ ጀመርን፣ እንመልሰዋለን፣ (መፈጸሙ) በኛ ላይ የሆነን ቀጠሮ ቀጠርን፣ እኛ (የቀጠርነውን) ሠሪዎች ነን።»[103]

አጥንቶች በሰበሰው ትቢያ ከሆኑ በኋላ እንደገና ተመልሰው ሕያው ሊሆኑ ይችላሉ ብለው ለሚጠራጠሩ ወገኖች የሚከተለው መልስ እንዲሰጣቸው ሊያዝ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿قل يحييها الذي أنشأها أول مرة، وهو بكل خلق عليم﴾ يس:٧٩

« ያ በመጀመሪያ ጊዜ (ከኢምንትነት) ያስገኛት ሕያው ያደርጋታል፣ እርሱም በፍጡር ሁሉ (ክንዋኔ) ዐዋቂ ነው፣ በላቸው።»[104]

<u>ሦስተኛ</u>:- ምንም ዓይነት ዕፅዋት የሌለበት ምድረበዳ መሬት ላይ ዝናም ዘንቦ ከሁሉም ዓይነት አረንጓዴ ተክል የለመለመበት ሕያው መሬት ይሆናል። ይህን ሕያውነት አላህ ደረቅ መሬት ሕያውና ለም መሬት ማድረግ የሚችል አምላክ ሙታንን እንደገና ለመቀስቀስ ቀላል ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ومن آياته أنك ترى الأرض خاشعة، فإذا أنزلنا عليها الماء اهتزت، وربت، إن الذي أحياها لمحيي الموتى، إنه على كل شيئ قدير﴾ فصلت:٣٩

102 አል-ሩም /30/: 27
103 አል-አንቢያ /21/: 104
104 ያሲን /36/: 79

﴿ ونزلنا من السماء ماء مباركا، فأنبتنا به جنات وحب الحصيد، والنخل باسقات لها طلع نضيد، رزقا للعباد، وأحيينا به بلدة ميتا كذلك الخروج.﴾ ق: ٩٠ - ٩٥

«አንተ ምድርን ደረቅ ኾና ማየትህም ከምልክቶቹ ነው፤ በርሷም ላይ ውሃን ባወረድን ጊዜ፤ (በበቃያዎችዋ) ትንቀሳቀሳለች፤ ትነፋለችም፤ ያ ሕያው ያደረጋት ጌታ በእርግጥ ሙታንን ሕያው አድራጊ ነው፤ እርሱ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነውና።»[105]

«ከሰማይም ብሩክን ውሃ አወረድን፤ በርሱም አትክልቶችንና የሚታጨደውን (አዝመራ) ፍሬ አበቀልን። ዘምባባንም ረዣዦችም፤ ለርሷ የተደራረበ እንቡጥ ያላት ስትኾን (አበቀልን)። ለባሮቹ ሲሳይ ትኾን ዘንድ (አበቀልናት)፤ በርሱም የሞተችን አገር ሕያው አደረግንበት፤ (ከመቃብር) መውጣትም እንደዚሁ ነው።»[106]

ከሐቅ ጎዳና ከተዛነፉ ሰዎች መካከል ከፊሉ የመቃብር ውስጥ ሲቃይንና ተድላውንም በማስተባበል ከተለመደው ሕግ ውጭ የሆነ ሊሆን የማይችል ነው፤ እንዴ መቃብር ቢከፈት እንደነበረ ሆና እናገኘዋለን እንጂ ለፋትም ይሁን ጥበት ጨምሮ አናገኘውም በሚል አባባል ጠመሙ።

ይህን አባባል ሸሪዓው ዝርዝራዊው ሁኔታና ሕሊናዊ ማስረጃ የሚያፈርስ ተባበሉት ትንፈት ነው።

የሸሪዓውን ማስረጃ በተመለከተ የመቃብር ውስጥ ሥቃይና ደስታ ለመኖራቸው በመጨረሻው ቀን ከማመን ሥር በሚጠቃለሉ ጉዳዮች ውስጥ በ«ለ» ውስጥ ቁርአናዊ አንቀጾችና ነቢያዊ ሐዲሶች ማስረጃዎችን ይታወሳል። በተጨማሪም የሚከተለውን ነቢያዊ ሐዲስ እናገኛለን:-

105 ሐ.ሚም አስሰጅዳህ /41/: 39
106 ቃፍ /50/: 9-11

( خرج النبي صلى الله عليه وسلم من بعض حيطان المدينة، فسمع صوت انسانين يعذبان في قبورهما.. لن أحدهما كان لا يستتر من البول ((وفى رواية من بوله)) ولن الآخر كان يمشى بالنميمة) رواه البخارى

« ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከመዲና አጥሮች ወጥተው ሁለት ሰዎች መቃብር ውስጥ ሲሰቃዩ ድምጻቸውን ሰሙ። ... አንደኛቸው ከሽንት የማይጠበቅ ነበር፣ ሌላኛው ደግሞ አሳባቂ (ሰውን የሚያጣላ ነገር አመላላሽ) ነበር።»[107]

ተጨባጩን ሁኔታ በተመለከተ ደግሞ አንድ ሰው ተኝቶ በሕልሙ በጣም ሰፊ በሆነ ቦታ ላይ ሆኖ ሊደሰትና ሊዝናና ሊያይ ይችላል። ወይም ጠባብ አስጨናቂና ሥቃይ በመላበት ቦታ ውስጥ ሊሰቃይ ሊያይ ይችላል። ምናልባትም አንዳንድ ጊዜ በሕልሙ ምክንያት ከእንቅልፉ የሚነሳበት ሁኔታም ይኖራል። ይህ ሁሉ ቢሆን ግን መኝታው ላይ እንደነበረ አቤቱ ውስጥ እንዳለ መሆኑ ይታወቃል። ሞትም የእንቅልፍ ወንድም ነው። አላህ (ሱ.ወ) ለዚህ ነው እንዲህ ያለው:-

﴿ الله يتوفى الأنفس حين موتها، والتى لم تمت فى منامها فيمسك التى قضى عليها الموت ويرسل الأخرى إلى أجل مسمى﴾ الزمر:٤٢

« አላህ ነፍሶችን በሞታቸው ጊዜ፣ ይወስዳል፣ ያችንም ያልሞተችውን በእንቅልፍ ጊዜ፣ (ይወስዳታል)፣ ታዲያ ያችን ሞትን የፈረደባትን ይይዛታል፣ ሌላይቱንም እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ ይለቃታል፣... »[108]

---

107 ቡኻሪ የዘገቡት ሐዲስ

ሕሊናዊ ማስረጃን በተመለከተ ደግሞ አንድ ሰው ተኝቶ ከነባራዊው ሁኔታ ጋር ሙሉ በሙሉ የተጣጣመ እውነተኛ ሕልም ያያል። ምናልባትም ነቢዩ ሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) እንዳሉ በዚህች ዓለማዊ ሕይወት በነበሩበት ጊዜ በነበራቸው አኳኋን ሆነው ያያቸዋል። ነቢዩን በዚህ ሁኔታ ያየ ሰው ደግሞ በትክክል ነቢዩን በእውን እንዳየ ይቆጠራል። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ሕልሙን ያየው ሰው እቤቱ ውስጥ መኝታው ላይ እንዳለ ሆኖ ነው። ይህ ሁኔታ በዓለማዊ ጉዳዮች ውስጥ የሚሆን እስከሆነ ድረስ ከወዲያኛው ዓለም ጉዳዮች ጋር በተያያዘ መልኩ የማይቻልበት ምን ምክንያት ይኖራል?

ሟቹ የተቀበረበት መቃብር ቢከፈት መቃብሩ ሰፋትም ሆነ ጥበት ሳያሳይ ልክ እንደነበረ ይታያል በሚለው አባባላቸው ላይ ለተመረኮዙት ከተለያዩ አንጻር ምላሽ ይሰጣቸዋል።

<u>አንደኛ</u>:- ሸሪዓው ያረጋገጠውን ነገር እንዲህ ባሉ ተራ ውዥንብሮች መቃወም አይፈቀድም። ተቃዋሚው ሰው ሸሪዓው ይዟቸው የመጣቸውን እውነታዎች በሚገባ ቢያስተውል ውዥንብሮቹ ውዳቂ መሆናቸውን ይረዳል።

<u>ሁለተኛ</u>:- የመቃብር ዓለም ሕይወት (በርዘኽ) ጉዳዮች ከሕዋሳዊ ግንዛቤ ውጭ የሆኑና በሰው ግንዛቤ ሥር ሊውሉ የማይችሉ ጉዳዮች ናቸው። እነዚህ ጉዳዮች ከሰው ግንዛቤ ሥር የሚውሉ ቢሆኑ ኖሮ ከሕሳዊ ዕውቀት በራቀው (በጓይብ) ማመን ጥቅም የለሽ በሆነ ነበር። ባላዩት ነገር በሚያምኑ ምዕመናንና በከሓዲዎች መካከልም ልዩነት ባልኖረ ነበር።

<u>ሦስተኛ</u>:- የመቃብር ውስጥ ሥቃይና ደስታን የመቃብሩን መስፋትና መጥበብ መረዳት የሚችለው ሟቹ ብቻ ነው። ልክ አንድ ሰው ተኝቶ አስደሳችና ሰፊ ቦታ ውስጥ ሆኖ ወይም ጠባብና አስጨናቂ ቦታ ውስጥ ሆኖ በሕልሙ ሲመለከት እንደሚሆነው ማለት ነው። ሌላው ሰው የተኛው

ግለሰብ እቤቱ ውስጥ መኝታው ላይ እንደነበረ ምንም ለውጥ ያላሳየ መሆኑን ነው የሚረዳው። ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ከአላህ (ሱ.ወ) ራእይ (ወሕይ) ሲተላለፍላቸው ከባልደረቦቻቸው (ከሰሓቦቹ) መካከል ሆነው ይሰሙ ነበር። ሰሓቦቹ ግን ምንም አይሰሙም ነበር። አንዳንድ ጊዜም መልአክ በሰው ተመስሉ ወሕዩን ያስተላልፍላቸዋል። ሰሓቦቹ ግን መልአኩን አያዩም፣ አይሰሙትም።

አራተኛ:- የሰዎች የግንዛቤ ደረጃ አላህ (ሱ.ወ) በሚሰጣቸው የግንዛቤ ደረጃ ብቻ የተገደበ ነው። ስለዚህ ሁሉንም ነገር ሊያውቁና ሊገነዘቡ አይችሉም። ሰባቱ ሰማያትና መሬት በውስጣቸው ያሉት ፍጥረታት በሙሉ አላህን (ሱ.ወ) ያጠራሉ፣ ያወድሳሉ። ይህን ውዳሴ አንዳንድ ጊዜ አላህ (ሱ.ወ) ከፍጡራን መካከል ለሻው ያሰማል። ይሁን እንጂ ይህ የፍጥረተ ዓለም ውዳሴ ከኛ ግንዛቤ ውጭ ነው። ይህንኑ በማስመልከት አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿تسبح له السماوات السبع والأرض ومن فيهن، وإن من شيئ

إلا يسبح بحمده، ولكن لا تفقهون تسبيحهم﴾ الاسراء: ٤٤

« ሰባቱ ሰማያትና ምድርም በውስጣቸውም ያለው ሁሉ ለርሱ ያጠራሉ፣ ከነገርም ሁሉ ከማመስገን ጋር የሚያጠራው ( የሚያወድሰው) እንጂ አንድም የለም፤ ግን ማጥራታቸውን አታውቁትም፤...»[109]

ሰይጣናትና ጋኔንም እንደዚሁ ምድር ላይ ይሄዳሉ ይመላለሳሉ። ጋኔኖች ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ ቀርበው ነቢዩ የሚያነቡትን ቁርአን ካዳመጡ በኋላ ወደ ወገኖቻቸው ተመልሰው የሰሙትን መልክተ እስላም አስተ

---

109 አል- ኢስራእ /17/: 44

108 አል- ዙመር /39/: 42

ባልፈዋል። ይህ ሁሉ ግን ከኛ ግንዛቤ ውጭ ነው። አላህ (ሱ.ወ) ይህንን በማስመልከት እንዲህ ብሏል:-

﴿ يا بنى آدم ليفتننكم الشيطان كما أخرج أبويكم من الجنة ينزع عنهما لباسهما ليريهما سوءاتهما، إنه يراكم هو وقبيله من حيث لاترونهم، إنا جعلنا الشياطين أولياء للذين لايؤمنون﴾

الأعراف: ٢٧

« የአዳም ልጆች ሆይ! ሰይጣን አባትና እናታችሁን ሀፍረተ ገላቸውን ሊያሳያቸው ልብሶቻቸውን ከነሱ የገፈፋቸው ሲኾን ከገነት እንዳወጣቸው ሁሉ እናንተን አይሞክራችሁ! እነሆ እርሱ ከነሰራዊቱ ከማታዩዋቸው ሥፍራ ያዩዋችኋልና! እኛ ሰይጣናትን ለእነዚያ ለማያምኑት ወዳጆች አድርገናል።» 110

ሰዎች ሁሉንም የተፈጠር ክስተት ከግንዛቤያቸው ሥር ማዋል የማይችሉ እስከሆኑ ድረስም ከሕዋሳት የራቁና በሸሪዓው የተረጋገጡ ጉዳዮችን ለራሳቸው ስለማይገነዘቡ ብቻ ማስተባበል አይፈቀድም።

---

110 አል- አዕራፍ /7/: 27

## በቀደር ማመን

በ «ቀደር» ማመን አላህ (ሱ.ወ) በነባር ዕውቀቱና በጥበቡ መሠረት በተፈጥሮ ውስጥ የሚከሰቱ ክስተቶችን በሙሉ ጥንቱን ወስኖ ማስቀመጡን ማመን ማለት ነው።

## በቀደር ማመን አራት ነጥቦችን ያጠቃልላል

<u>አንደኛ</u>:- አላህ (ሱ.ወ) ነገሮችን ሁሉ ከራሱ ሥራዎች ጋር የተያያዙትንም ሆነ ከፍጡራት ጋር የተሳሰሩትን በጥቅሉና በዝርዝር መጀመሪያና መጨረሻ በሌለው ሁኔታ የሚያውቅ መሆኑን ማመን።

<u>ሁለተኛ</u>:- ይህን ሁሉ አላህ (ሱ.ወ) በተጠበቀው ሰሌዳ (ለውሑል መሕፉዝ) ላይ የጻፈው መሆኑን ማመን።

እነዚህን ሁለት ነጥቦች አስመልክቶ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ ألم تعلم أن الله يعلم ما في السماوات والأرض، إن ذلك في كتاب، إن ذلك على الله يسير ﴾ الحج: ٧٠

« አላህ በሰማይና በምድር ውስጥ ያለን ሁሉ በእርግጥ የሚያውቅ መኾኑን አታውቅምን? ይህ በመጽሐፍ ውስጥ /የተመዘገበ/ ነው፤ ይህ በአላህ ላይ ገር ነው።» [111]

ሙስሊም ዐብደላህ ብን ዐምር ብን አልዓስን በመጥቀስ በዘገቡት መሠረት ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

« كتب الله مقادير الخلائق قبل ان يخلق السماوات والأرض بخمسين الف سنة »

رواه مسلم

« አላህ የፍጥረታትን ወሰኖች ሰማያትንና መሬትን ከመፍጠሩ ከሃምሳ ሺህ ዓመት ቀደም ብሎ ነው የጻፈው (የወሰነው)።» [112]

ሦስተኛ:- ከአላህ ሥራ ጋር የተያያዙም ሆነ ከፍጡራን ድርጊት ጋር የተያያዙ ክስተቶች በሙሉ በአላህ (ሱ.ወ) ፈቃድና በርሱ መሻት ብቻ የሚፈጸሙ መሆናቸው ማመን። አላህ (ሱ.ወ) ከራሱ ሥራ ጋር የተያያዘውን አስመልክቶ እንዲህ ብሏል:-

﴿وربك يخلق ما يشاء ويختار﴾ القصص:٦٨

﴿ويفعل الله ما يشاء﴾ إبراهيم:٢٧

﴿هو الذى يصوركم فى الأرحام كيف يشاء﴾ آل عمران:٦

« ጌታህም የሚሻውን ይፈጥራል፤ ይመርጣልም፤ ለነሱ (ለሰዎች) ምርጫ የላቸውም፤...» [113]

« ... አላህም የሚሻውን ይሠራል።» [114]

« እርሱ ያ በማሕጸኖች ውስጥ እንደሚሻ አድርጎ የሚቀርጻችሁ ነው።...» [115]

---

111 አል- ሐጅ /22/:70
112 ሙስሊም የዘገቡት ሐዲስ
113 አል-ቀሶስ /28/: 68
114 ኢብራሂም /14/: 27
115 አሊ-ዒምራን/3/:6

የፍጡራን ሥራ አስመልክቶ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ولو شاء الله لسلطهم عليكم فلقاتلوكم﴾ النساء:٩٠

«.. አላህም ቢሻ ኖሮ በእናንተ ላይ ኃይል በሰጣቸውና በተጋደሉዋችሁም፤»[116]

﴿ولو شاء الله ما فعلوه فذرهم وما يفترون﴾ الأنعام:١٣٧

«... አላህም ቢሻ ኖሮ ባልሠሩት ነበር፤ ከቅጥፈታቸውም ጋር ተዋቸው።»[117]

<u>አራተኛ</u>:- ፍጥረታት በሙሉ በማንነታቸው በባህሪያቸውና በአጠቃላይ እንቅስቃሴያቸው ሁሉ የአላህ (ሱ.ወ) ፍጡራን መሆናቸውን ማመን። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿الله خالق كل شيئ وهو على كل شيئ وكيل﴾ الزمر:٦٢

﴿وخلق كل شيئ فقدره تقديرا﴾ الفرقان:٢

«አላህ የነገሩ ሁሉ ፈጣሪ ነው። እርሱም በነገሩ ሁሉ ላይ አስተናባሪ ነው።»[118]

«... ነገሩንም ሁሉ የፈጠረና በትክክልም ያዘጋጀ ነው።»[119]

ነቢዩ ኢብራሂም (ሰ.ዐ.ወ) ለሕዝባቸው የሰጡትን መልስ በመጥቀስ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿والله خلقكم وما تعملون﴾ الصافات:٩٦

116 አል-ኒሳእ/4/: 90
117 አል- አንዓም /6/. 137
118 አል-ዙመር /39/: 62
119 አል- ፉርቃን /25/: 2

« አላህ እናንተንም የምትሠሩትንም የፈጠረ ሲሆን።» [120]

ከላይ በገለጽነው መሠረት በቀደር ማመን አንድ ሰው በፍላጐቱ በሚፈጽማቸው ድርጊቶች ላይ ወሳኙና ችሎታ ያለው መሆኑን አይጻረርም። ሸሪዓውና ነባራዊ ሁኔታ የዚህን አንጻራዊ ነጻነት ወሳኝነት ያረጋግጡ ለታልና።

የሸሪዓውን ማረጋገጫ በተመለከተ ስለሰው ፍላጐት አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿فمن شاء اتخذ الى ربه مآبا﴾ النبأ

﴿فأتوا حرثكم أنى شئتم﴾ البقرة:٢٢٣

« .. የሻውም ሰው ወደጌታው መመለስን ይይዛል።» [121]

« ... እርሻችሁንም በፈለጋችሁት ኹኔታ ድረሱ፣..» [122]

ችሎታን አስመልክቶም አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿فاتقوا الله ما استطعتم واسمعوا وأطيعوا﴾ التغابن:١٦

﴿لايكلف الله نفسا إلا وسعها، لها ماكسبت وعليها ما اكتسبت﴾

البقرة:٢٨٦

« አላህንም የቻላችሁትን ያክል ፍሩት፣ ትዕዛዙን ስሙም፣ ታዘዙም፣ ...» [123]

« አላህ ነፍስን ከችሎታዋ በላይ አያስገድዳትም፣ ለርሷ የሠራችው አላት። በርሷም ላይ ያፈራችው (ኃጢአት) አለባት። ... » [124]

---

120 አስ- ሷፋት /37/: 96
121 አል-ነባእ /78/: 39
122 አል- በቀራህ /2/: 223
123 አት-ተጋቡን /64/: 16
124 አል- በቀራህ /2/: 286

ነብራዊውን ማስረጃ በተመለከተ ደግሞ ግንኙነውም ሰው በፍላጐቱ የመሥራት የመተው ነጻነትና መሻት ወይም ውሳኔና ፍላጐት ያለው መሆኑን ያውቃል። በፍላጐቱ የሚፈጽማቸውን እንደ መሄድ ያለውንና ከፍላጐቱ ውጭ የሚከሰተውን እንደ መንቀጥቀጥ ያለውን የሚለየውም በዚሁ የመሻት ነጻነት ነው። ይሁን እንጂ ያንድ ሰው ፍላጐት ወይም ግሻትና ችሎታው በአላህ (ሱ.ወ) መሻትና ችሎታ ብቻ የሚከሰቱ ናቸው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏልና:-

﴿لمن شاء منكم أن يستقيم، وما تشاؤن إلا أن يشاء الله رب العالمين﴾ التكوير:٢٨ - ٢٩

« ከናንተ ቀጥተኛ መሆንን ለሻ ሰው (መገሠጫ ነው)። የዓለማት ጌታ አላህ ካልሻም አትሹም»» [125]

ዩኒቨርስ በሙሉ የአላህ ንብረትና ግዛቱ በመሆኑ በግዛቱ ውስጥ ከርሱ ዕውቀትና መሻት ውጭ የሚሆን ምንም አይኖርም።

ከላይ በገለጽነው መሠረት በቀደር ማመን አንድ ሰው ግዴታዎቹን ለመተው ወይም ኃጢአት ለመሥራት ማመካኛና ማስረጃ ሊሆን አይችልም። ስለዚህም በዚህ ማመካኘቱ በተለያዩ መንገዶች ውድቅ ነው:-

<u>አንደኛ</u>:- አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿سيقول الذين أشركوا لو شاء الله ما أشركنا ولا آباؤنا ولا حرمنا من شيء، كذلك كذب الذين من قبلهم حتى ذاقوا بأسنا

125 አል- ተክዊር /81/: 28- 29

﴿قل هل عندكم من علم فتخرجوه لنا؟ ان تتبعون إلا الظن وان أنتم إلا تخرصون﴾ الأنعام:١٤٨

« እነዚያ ያጋሩት፣ አላህ በሻ ኖሮ እኛም አባቶቻችንም ባላጋራን ነበር፣ እንዳችንም ነገር እርም ባላደረግን ነበር፣ ይላሉ፣ እንደዚሁ (እነዚህ እንደሚሉት) እነዚያ ከበፊታቸው የነበሩት፣ ብርቱ ቅጣታችንን እስከ ቀመሱ ድረስ አስተባበሉ፣ ለኛ ታወጡልን ዘንድ (ማጋራታችሁን ለመውደዱ) እናንተ ዘንድ ዕውቀት አለን? ጥርጣሬን እንጅ ሌላ አትከተሉም፣ እናንተ ዋሾዎች እንጂ ሌላ አይደላችሁም በላቸው።»[126]

በቀደር (በአላህ መሻት) ማመካኘታቸው ተቀባይነት ቢኖረው ኖሮ አላህ ቅጣቱን ባላቀመሳቸው ነበር።

<u>ሁለተኛ</u>:- አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿رسلا مبشرين ومنذرين لئلا يكون للناس على الله حجة بعد الرسل وكان الله عزيزا حكيما﴾ النساء:١٦٥

« ከመልክተኞቹ በኋላ ለሰዎች በአላህ ላይ አስረጅ እንዳይኖር፣ አብሳሪዎችና አስፈራሪዎች የሆኑን መልክተኞች (ላክን)፣ አላህም አሸናፊ ጥበበኛ ነው።»[127]

ቀደር ለአጥፊዎች (ለሕግ ተላላፊዎች) ማመካኛ አስረጅ ቢሆን ኖሮ መልክተኞች በመላካቸው ውድቅ ባልተደረገ ነበር። ከነዚያም መላክ በኋላ የተፈጸመው ጥፋትም በአላህ መሻት የተከሰተ ነውና።

---

126 አል- አንዓም /6/: 148
127 አል- ኒሳእ /4/: 165

__ሃዲስ፲፫__:- ቡኻሪና ሙስሊም ዐሊይ ብን አቢ ጧሊብን በመጥቀስ የዘገቡት ቀጥሎ የተመለከተው የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሐዲስ:-

( ما منكم من أحد إلا قد كتب مقعده من النار أو من الجنة.
فقال رجل من القوم: ألا نتكل يا رسول الله؟ فقال: لا اعملوا
فكل ميسر، ثم قرأ) :

« ከናንተ መካከል መቀመጫው ከእሳት ውስጥ ወይም ከገነት ውስጥ ያልተጻፈ (ያልተወሰነ) አንድም ሰው የለም። የአላህ መልክተኛ ሆይ! በዚያው በተወሰነው ላይ ተመርኩዘን እንቀመጥ ወይ? ብሎ ከተሰበሰበው መካከል አንድ ሰው ሲጠይቅ:- « የለም ሥሩ! ሁሉም ለተፈጠረለት ነገር የተገራ (የተመቻቸ) ነውና።

አሉና የሚከተለውን የአላህ ቃል አነበቡ:-

﴿فأما من أعطى واتقى﴾ الليل:١٨

« ያ የሚፈራና ችና ገንዘቡን (ሷደቆች) የሚሰጠው።»[128]

በዚህም ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሁሉም ሰው ግዴታውን እንዲፈጽም በማዘዝ በቀደር ማመካኘትን ከለከለዋል።

---

128 አል-ለይል /92/: 18

__አራተኛ__:- አላህ (ሱ.ወ) ባሪያውን ይህን ሥራ ይህን አትሥራ ብሎ አዞታል። ያዘዘውም የሚችለውን ብቻ ነው። እንዲህ በማለት:-

﴿ فاتقوا الله مااستطعتم ﴾ التغابن:١٦

﴿ لايكلف الله نفسا إلا وسعها ﴾ البقرة:٢٨٦

« አላህንም የቻላችሁትን ያክል ፍሩት፤ ... »[129]

« አላህ ነፍስን ከችሎታዋ በላይ አያስገድዳትም፤... »[130]

አንድ የአላህ ባሪያ በሥራዎቹ ላይ ተገዳጅ (ምንም የመሥራትና የመተው ነጻነት የሌለው) ቢሆን ኖሮ ሊወጣው የማይችል ከአቅሙ በላይ የሆነ ግዴታ በተጣለበት ነበር። ይህ ደግሞ መሠረት የሌለው ውድቅ ነገር ነው። ስለዚህም ባለማወቅ ወይም በመዘንጋት ወይም ተገዶ ኃጢአት ቢፈጽም ምክንያት አለውና አይጠየቅበትም።

__አምስተኛ__:- የአላህ ቀደር (መሻት) ነገሩ ከተከሰተ በኋላ ብቻ የሚታወቅ ድብቅ ምስጢር ነው። ያንድ ሰው ፍላጐት (ውሳኔ) አንድን ሥራ የሚቀድም በመሆኑ ያን ሥራ ለመሥራት ያለው ፍላጐት የአላህን ቀደር በማወቅ ላይ የተመሠረተ አይደለም። በዚህም በቀደር ማመካኘቱ ይወገዳል። በማያውቁት ነገር ማመካኘት ወይም የማያውቁትን በአስረጅነት ማቅረብ አይቻልምና።

__ስድስተኛ__:- የሰው ልጅ በዓለማዊ ጉዳዮቹ የሚስማማውን ለማግኘት ሲጓጓና የሚስማማውን ትቶ ወደማይስማማው የማይዞር መሆኑን እንመለከታለን። በዚህ በኩል በቀደር አያመካኝም። በሃይማኖታዊ ጉዳዮች ውስጥ ግን ከሚጠቅመው ነገር ወደሚጐዳው ነገር በመዞር በቀደር ለምን ያመካኛል? ሁለቱ ነገሮች አንድ ዓይነት አይደሉምን?!

---

129 አል-ተጋቡን /64/: 16
130 አል- በቀራህ /2/: 286

ይህን የሚያብራራ ምሳሌ እነሆ:- አንድ ሰው ሁለት መንገዶች ፍርት አንደኛው ግድያ፣ ዝርፊያ ፣ የመብቶች መደፈር፣ ፍርሃትና ረሃብ ወደ ሰፈነበትና ሙሉ በሙሉ ሥርዓተ አልበኝነት ወደ ነገሠበት አገር የሚወስድ መንገድ ነው። ሁለተኛው መንገድ ደግሞ ሙሉ በሙሉ ሥነ ሥርዓት ወደሰፈነበት፣ ጸጥታው የተረጋጋ፣ የተደላደለ ኑሮ የሚገኝበት የሰው ሕይወት ክብሩና ንብረቱ ወደሚከበርበት አገር የሚያደርስ መንገድ ነው። ከሁለቱ መንገዶች የትኛውን ነው የሚይዘው?

ሥነ ሥርዓትና ጸጥታ ወዳለበት የሚወስደውን መንገድ ነው የሚይዘው። ጤነኛ አእምሮ ያለው ሰው ሥርዓተ አልበኝነትና ስጋት ወዳለበት አገር የሚወስደውን መንገድ ይዞ በቀደር ሊያመካኝ በፍጹም አይችልም። ታዲያ በወዲያኛው ሕይወት (በአኺራ) ነገር የገነትን መንገድ ትቶ የእሳት ጉዳና በመምረጥ በቀደር ለምን ያመካኛል?

ሌላ ምሣሌ:- አንድ ሕመምተኛ መድኃኒት ይታዘዝለትና ሳይወድ በግድ ይጠጠዋል። ከሚጎዱት የምግብ ዓይነቶች ይከለከልና እያስፈለገውና ነፍሱ እየጅመጀች ይተወዋል። ይህ ሁሉ ለመዳንና ጤነኛ ለመሆን ሲባል ነው። በቀደር በማመካኘት ግን መድኃኒቱን ከመውሰድ አይታቀብም፤ ወይም የተከለከለውን ጎጂ የምግብ ዓይነት አይበላም። ታዲያ የሰው ልጅ አላህና ነቢዩ ያዘዙትን በቀደር በማመካኘት ለምን ይተዋል? የከለከሉትንም በቀደር በማሳበብ ለምን ይፈጽማል?

<u>ሶስተኛ</u>:- ግዴታዎችን በመተው ወይም ኃጢአቶችን በመፈጸም በቀደር የሚያመካኘው ሰው፤ ሌላ ሰው ጥቃት ፈጽሞበት ገንዘቡን ቢወስድበት ወይም መብቱን ደፍሮ በቀደር ቢያሳብብና አትውቀሰኝ ግፍ የፈጸምኩብህ በአላህ ቀደር ነው ቢለው ምክንያቱን አይቀበልም። ታዲያ ሌላ ሰው በዋለበት ግፍና የመብት መዳፈር ሁኔታ በቀደር ማሳበቡን የማይቀበል እስከሆነ ድረስ እሱ ራሱ የአላህን (ሱ.ወ) መብት ተጋፍቶ ቀደርን በማመካኘት እንዴት ያቀርባል?!

የምዕመናን አሚር ዑመር ብን አልኸጧብ እጁ ሊቆረጥ የሚገባ ሌባ ተይዞ ቀረበላቸውና እጁ እንዲቆረጥ ያዛሉ። የምዕመናን አሚር ሆይ! ይቆዩኝ! እኔ የሰረቅሁት በአላህ ቀደር ነው አላቸው። ዑመርም:- እኛም የምንቆርጠው በአላህ ቀደር ነው ማለታቸው ይነገራል።

## በቀደር ማመን ከሚያስገኛቸው ጥቅሞች መካከል

<u>አንደኛ</u>:- ሳቢያዎችን በመመርኮዝ ለሥራ ሲነሱ፣ ሁሉም ነገር በአላህ ቀደር (ውሳኔ) ብቻ የሚፈጸም በመሆኑ በሳቢያዎቹ ብቻ ላይ ላይተማመኑ በአላህ (ሱ.ወ) ላይ መተማመን።

<u>ሁለተኛ</u>:- አንድ ሰው የፍላጐቱን አግኝቶ ሲሳካለት በራሱ ብቃት አለመኩራራትና አለመመጻደቅ። ስኬቱ ከአላህ (ሱ.ወ) በተገኘ ጸጋ እርሱ በወሰነው የድልና የበጐ ሳቢያዎች ውጤት ነውና። ራስን በራስ ማሞካሸትና ራሱን ማኩራራት ይህን የአላህ ጸጋ እንዳያመሰግን ያዘናጋዋል።

<u>ሦስተኛ</u>:-በአላህ መሻትና በውሳኔዎቹ (በቀደር) ከሚፈጸሙት ጉዳዮች አንጻር የሚወደው ነገር ስለአመለጠው ወይም የማያስደስት ነገር ስለደረሰበት ሳይጨነቅ እርጋታና የሕሊና ዕረፍት ማስገኘት።የሰማያትና የምድሩ ንግሥና የገሉ በሆነው አላህ ውሳኔ የተፈጸመና ወደድንም ጠላንም የግዴታ መፈጸም ያለበት ነገር ነውና። ይህንኑ በማስመልከት አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል: ﴿ما أصاب من مصيبة فى الأرض ولا فى أنفسكم إلا فى كتاب من قبل أن نبرأها إن ذلك على الله يسير، لكيلا تأسوا على ما فاتكم ولا تفرحوا بما آتاكم والله لا يحب كل مختال فخور﴾

الحديد: ٢٢ - ٢٣

«በምድርም፣ በነፍሶቻችሁም፣ መከራ (ማንኛይም) አትነካም፣ ሳንፈጥራት በፊት በመጽሐፍ የተመዘገበች ብትኾን እንጂ፤ ይህ በአላህ ላይ ገር ነው።(ይህ ማሳወቃችን) በአመለጣችሁ ጸጋ ላይ እንዳታዝኑ፣ አላህም በሰጣችሁ ነገር (በትዕቢት) እንዳትደሰቱ ነው፤ አላህም ኩራተኛን፣ ጉረኛን ሁሉ አይወድም።»[130]

ነቢዩም (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ይላሉ:-

(عجبا لأمر المؤمن ان أمره كله خير، وليس ذلك لأحد إلا لمؤمن إن أصابته سراء شكر فكان خيرا له، وان أصابته ضراء صبر فكان خيرا له) رواه مسلم

«የአማኝ (ሙእምን) ሰው ነገር አስደናቂ ነው። ሁሉም ነገሩ በጎ (መልካም ጎን ያለው) ነውና። ይህም የአማኙ (ባህሪ) እንጂ የሌላ የማንም አይደለም። የሚያስደስት ነገር ሲገጥመው (አላህን) ያመሰግንና ጥሩ ይሆንለታል። ክፉ ነገር ሲደርስበትም ይታገስና (ትዕግሥት) ጥሩ ይሆንለታል።»[131]

በቀደር ግመን አስመልክተው ሁለት ቡድኖች ተሳስተዋል:-

<u>አንደኛው:-</u> አንድ የአላህ ባሪያ በሚሠራቸው ነገሮች ላይ የራሱ የሆነ ፍላጎትና ችሎታ (ኃይል) የሌለው ተገዳጅ ነው ያሉና «ጀበሪያ» በመባል የሚታወቅ ቡድን፤

<u>ሁለተኛ:-</u> አንድ የአላህ አገልጋይ በሚፈጽማቸው ሥራዎች ሁሉ የራሱ የሆነ ነጻ ፍላጎት (ውሳኔ) እና ኃይል ያለው ሲሆን፤ የአላህ (ሱ.ወ) ፍላጎት (መሺአህ) እና ችሎታው በግለሰቡ ተግባር ላይ ሚና (ተጽእኖ) የለውም የሚሉ «ቀደሪያ» በመባል የሚታወቅ ቡድን፤

131 መስሊም የዘገቡት ሐዲስ

## ለመጀመሪያው ቡድን ለ «ጀበሪያ» የሚሰጥ የሸሪዓና የተጨባጭ እውነታ ምላሽ

<u>ሸሪዓን በተመለከተ</u>:- አላህ (ሱ.ወ) አንድ አገልጋዩ ፍላጎት (መሺአህ) እንዳለው በማረጋገጥ ሥራውን ከሥራው ጋር አያይዟል። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿منكم من يريد الدنيا ومنكم من يريد الآخرة﴾

آل عمران:١٥٢

﴿وقل الحق من ربكم فمن شاء فليؤمن، ومن شاء فليكفر، إنا أعتدنا للظالمين نارا أحاط بهم سرادقها﴾ الكهف:٢٩

﴿من عمل صالحا فلنفسه، ومن أساء فعليها وما ربك بظلام للعبيد﴾ فصلت:٤٦

«... ከናንተ ውስጥ ቅርቢቱን ዓለም የሚሻ አለ፤ ከናንተ ውስጥም መጨረሻይቱን ዓለም የሚሻ አለ፤ ...» [133]

« :- እውነትም፥ ከጌታችሁ ነው፤ የሻም ሰው ይመን፤ የሻም ሰው ይካድ፤ በላቸው፤ እኛ ለበደለኞች አጥርዋ በነሱ የከበበ የኾነችውን እሳት አዘጋጅተናል፤ ...» [134]

« መልካም የሰራ ሰው ለነፍሱ ነው፤ ያጠፋም ሰው፤ በርሷ ላይ ነው፤ ጌታህም ለባሮቹ በዳይ አይደለም።» [135]

---

133 አል-ዒምራን/3/: 152
134 አል-ከሀፍ /18/: 29
135 ፊ.ሚም አል-ሰጅዳህ /41/: 46

<u>ተጨባጩን እውነታ በተመለከተ</u>:- ማንኛውም ሰው በራሱ ፍላጎት በሚፈጽማቸው እንደ መብላት፣ መጠጣት፣ መግዛትና መሸጥ ባሉት ድርጊቶቹና ከፍላጎቱ ውጭ በሚከሰቱት በመባ ምክንያት እንደ መንቀጥቀጥና ከጣራያ መውደቅ በመሳሰሉት ድርጊቶች መካከል ያለውን ልዩነት ያውቃል። በመጀመሪያው ሁኔታ ሳይገደድ በምርጫውና በፍላጎቱ እድራጊ ነው። በሁለተኛው ሁኔታ ደግሞ ድርጊቱ በምርጫውና በፍላጎቱ የተከሰተ አይደለም።

## ለሁለተኛው ቡድን ለ «ቀደሪያ» የሚሰጥ የሸሪዓና የአእምሮ መልስ

<u>ሸሪዓን በተመለከተ</u>:- አላህ (ሱ.ወ) የማንኛውም ነገር ፈጣሪ ነው። ሁሉም ነገር የሚሆነው በርሱ መሻት (በመሺአው) ነው። የአገልጋይ ፍጡራን ሥራዎች የሚከሰቱት በርሱ ፍቃድና ፍላጎት መሆኑን በመግለጽ አላህ (ሱ.ወ) መጽሐፉ ውስጥ እንዲህ ብሏል:-

﴿ولو شاء الله ما اقتتل الذين من بعدهم من بعد ماجاءتهم البينات، ولكن اختلفوا فمنهم من آمن ومنهم من كفر، ولو شاء الله ما اقتتلوا ولكن الله يفعل ما يريد﴾ البقرة:٢٥٣

﴿ولو شئنا لآتينا كل نفس هداها، ولكن حق القول مني لأملأن جهنم من الجنة والناس أجمعين.﴾ السجدة:١٣

---

« ... አላህም በሻ ኖሮ፤ እነዚያ ከነርሱ (ከመልክተኞቹ) በኋላ የነበሩት፤ ግልጽ ታምራቶች ከመጡላቸው በኋላ ባልተጋደሉ ነበር፤ ግን ተለያዩ፤ ከነርሱም ውስጥ የካደ ሰው አለ፤ አላህም በሻ ኖሮ ባልተዋጉ (ባልተለያዩ) ነበር፤ ግን አላህ የሚሻውን ይሠራል።»[136]

« በሻንም ኖሮ ነፍስን ሁሉ ቅንነቷን (እምነቷን) በሰጠናት ነበር፤ ግን ገሀነምን ከአጋንንትና ከሰዎች የተሰበሰቡ ኾነው በእርግጥ እሞላለሁ፣ ማለት፤ ቃሉ ከእኔ ተረጋገጠ።»[137]

<u>ለአምሮገን በተመለከተ</u>:- ቁንጮርስ በአጠቃላይ የአላህ ንብረት ነው። የዚህ ቁንጮርስ አካል የሆነው የሰው ልጅም የአላህ (ሱ.ወ) ንብረት ነው። ተገኘው ንብረት ደግሞ በገኘው ባለንብረት ሀብት ላይ ከባለቤቱ ፍቃድና ፍላጐት (መሺአህ) ውጭ ሊያዝበት አይችልም።

## የእስላማዊ እምነት (ዐቂዳ) ዓላማዎች

የእስላማዊው እምነት (ዐቂዳ) ዓላማዎች ማለት ፍላጐቶቹና እምነቱን ከመያዙ ጀርባ የሚያልማቸው ውድ ግቦቹ ናቸው። ዓላማዎቹ ብዙና የተለያዩ ዓይነቶች ሲሆኑ ከነዚህም የሚከተሉትን እናገኛለን:-

<u>አንደኛ</u>:- ፍጹማዊ በሆነ ፍላጐት አላህን (ሱ.ወ) ብቻ መገዛት። እርሱ ሸሪክ የሌለው ብቸኛ ፈጣሪ በመሆኑ ዓላማንና መገዛትን (ዐባዳን) ለርሱ ብቻ ማድረግ ግዴታ ነው።

<u>ሁለተኛ</u>:- አእምሮና ፍክሬን ይህ ዐቂዳ ከልቦና በመጥፋቱ ምክንያት ከሚከሰተው ሥርዓተ አልባ መደናበር ነጻ ማውጣት። ልቡ ከዚህ እምነት ባዶ የሆነ ሰው ወይ ልቡ ከሁሉም ዓይነት እምነት ባዶ ሆኖ ተጨባጩን ቁስ

---

136 አል-በቀራህ/2/: 253
137 አስ-ሰጅዳህ /32/: 13

አካል ብቻ የሚያመልክ ነው፡ ወይ ደግሞ በተሳሳቱ እምነቶችና አፈ-ተረቶች ውስጥ የሚደናበር ነው።

<u>ሦስተኛ</u>:- የሕሊናና የአመለካከት ደስታ ማስገኘት። በዚህ ዐቂዳ ያመነ ሰው የሕሊና ጭንቀትም ሆነ የአመለካከት መምታታት የለበትም። ዐቂዳው አማኙን ከፈጣሪው ስለሚያገናኘው አቀናባሪ ጌትነቱንና ሕግ ሰጭ አስተዳዳሪነቱ ወዶ በመቀበል ልቡ በአላህ ውሳኔ (ቀደር) ይረካል። በእስላም ጸንቶ ሌላ መተኪያ የማይፈልግ ይሆናል።

<u>አራተኛ</u>:- አላህን በመገዛት (በዕባዳና) ከሰዎች ጋር ባለው ማህበራዊ ግንኙነት ዓላማና ተግባርን ከስህተቶች ነጻ ማድረግ። ከእምነቱ መሠረቶች መካከል በመልክተኞች (በሩሱል) ማመን አንዱ በመሆኑና ይህም በተራው በዓላማም ሆነ በተግባር ንጹሕ የሆነውን ፈለጋቸውን መከተል ስለሚያ ጠቃልል ነው።

<u>አምስተኛ</u>:- በነገሮች ሁሉ ውስጥ ቁርጠኛና ትጉህ በመሆን፡ የመልካም ሥራ አጋጣሚን የአላህን ምንዳ /ሰዋብ/ በማሰብ ሳይጠቀሙ እንዳያመልጥ ማድረግ። የሚያስከትለውን ቅጣት በመፍራትም የኃጢአት አዝማሚያ ባዩ ቁጥር ከሥፍራው መራቅ። ከእምነቱ መሠረቶች አንዱ ደግሞ ከሞት ተቀስቅሶ በሠሩት ሥራ ዓይነት ተመጣጣኝ ዋጋ የሚሰጥ መሆኑን ማመን ነውና። አላህ /ሱ.ወ/ እንዲህ ብሏል:-

﴿ولكل درجت مما عملوا، وما ربك بغافل عما يعملون﴾

الأنعام:١٣٢

« ለሁሉም ከሠሩት ሥራ /የተበላለጡ/ ደረጃዎች አሏቸው፤ ጌታህም ከሚሠሩት ሁሉ ዘንጊ አይደለም።»[138]

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ቀጥሎ በተመለከተ ሐዲስ ለዚሁ ዓላማ ገፋፍተዋል:-

---

138 አል- አንዓም /6/: 132

( المؤمن القوي خير وأحب إلى الله من المؤمن الضعيف، وفي كل خير أحرص على ما ينفعك واستعن بالله، ولا تعجز، وإن أصابك شيئ فلا تقل لو أني فعلت كان كذا وكذا ولكن قل: قدر الله وما شاء فعل، فإن لو تفتح عمل الشيطان) رواه مسلم

«ጠንካራ አማኝ ከደካማው አማኝ ይበልጥ አላህ ዘንድ በላጭና የተወደደ ነው። በሁሉም ዘንድ ደግ ነገር አለ። ለሚጠቅምህ ነገር ጓጉተህ (ተጋተህ) ከአላህ ረድኤት ጠይቅ። ደካማ አትሁን። አንድ ችግር ቢደርስብህ እንዲህ ባደርግ እንደዚያ ቢሆን ኖሮ እንዲህ ባሆን ነበር አትበል። አላህ ወሰነ፣ እርሱ የሻውን ሠራ በል እንጂ። ‹ቢሆን ኖሮ› የሰይጣንን ሥራ ትከፍታለችና።»[139]

ስድስተኛ:- ሃይማኖቱን ለማረጋገጥና ማዕዘናቱን ለማጠናከር ማንኛውንም ውዱንም ርካሹንም ነገር ሁሉ ለሚሰዋ፣ በዚህ ረገድ ለሚደርስበት ችግር ግድ የሌለው ጠንካራ ሕዝብ መመሥረት። ይህን አስመልክቶ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿ إنما المؤمنون الذين آمنوا بالله ورسوله ثم لم يرتابوا وجاهدوا بأموالهم وأنفسهم في سبيل الله أولئك هم الصادقون﴾ الحجرات:١٥

(እውነተኞቹ) ምእመናን፣ እነዚያ በአላህና በመልክተኛው ያመኑት፣ ከዚያም ያልተጠራጠሩት፣ በገንዘቦቻቸውና በነፍሶቻቸውም በአላህ መንገድ የታገሉት ብቻ ናቸው፤ እነዚያ እነሱ እውነተኞቹ ናቸው።[140]

139 ሙስሊም የዘገቡት ሐዲስ
140 አል- ሑጁራት /49/: 15

ሰባተኛ:- ግለሰቦችንና ህብረተሰቦችን በማሻሻል ምንዳና ክቡሩን ሁሉ በማቀዳጀት በዛሬይቱ ቅርቢቷ ዓለምና በመጪው ዘለዓለማዊ ሕይወት ለተድላ መብቃት። ይህን አስመልክቶ አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ብሏል:-

﴿من عمل صالحا من ذكر او انثى وهو مؤمن فلنحيينه حياة طيبة، ولنجزينهم اجرهم باحسن ما كانوا يعملون﴾ النحل:٩٧

« ከወንድ ወይም ከሴት፣ እርሱ አማኝ ኾኖ በጎን የሠራ፣ መልካም ኑሮን በእርግጥ እናኖረዋለን፣ ይሠሩትም ከነበሩት ነገር በመልካሙ ምንዳቸውን እንመነዳቸዋለን።» [141]

እነዚህ እንግዲህ ከእስልምና ዓቢይ ዓላማዎች ከፊሎቹ ሲሆኑ አላህ (ሱ.ወ) ለኛና ለሙስሊሞች በሙሉ ዓላማዎቹን እውን እንዲያደርግልን እንመኛለን።

---

141 አል- ነሕል /16/: 98

## የ1436 ዓ\ሀ 17ኛ የሮመዷን እስላማዊ የውድድር ጥያቄዎች አስመልክቶ የወጣ ማስታወቅያ።

1 ጥያቄዎቹ <u>ከእምነት መሰረቶች ትንታኔ</u> ከተባለው መጽሃፍ የተዘጋጁ ስሆን ሁሉም መመለስ አለበት።

2 መልሱን ረብዋህ በምገኘው የደዕዋ ቢሮ በአካል በማምጣት፤ ወይም በመ\ሣ\ቁ\ 29465 ሪያድ 11457፤ ወይም በመከተቡ የእሜል አድራሻ jaliyat@islamhouse.com እስከ 29|11|1436 ዓ|ሀ መልሱን ማስገባት ያስፈልጋል።

3 ትክክለኛ ስም ፓስፖርት፣ ኢቃማና መታወቂያ ላይ እንደሰፈረው መጻፍ አለበት፤ ከዚህ ጋር የተለየ ስም ይዞ የቀረበ ተወዳዳሪ አንቀበልም።


4 ስም፣ ቋንቋ፣ አድራሻ፣ ኢሜል፣ የስልክና የሞባይል ቁጥሮች መጻፍ አለባቸው።

5 የአሸናፊዎች ስም በወርሀ ሙሀረም 1437 ዓ\ሀ ረብዋ በምገኘው የደዕዋ ጽ\ቤት በማስታወቅያ ይወጣል፣ በመከተቡ ዌብሳይትም www.islamhouse.com ይወጣል። በመከተቡ ሶሻል ሚድያ ገጽ ላይም ይወጣል።

6 የውድድሩ አሸናፊዎች የደስታ መግለጫ በስልክ ይተላለፍላቸዋል።

7 የግብዣ ቀንም ቀጥሎ ይገለጻል።በሶሻል ሚድያ ላይም ይወጣል።

8 መልሱ ንጹህ ወረቀት ላይ ግልጽ በሆነ ጽሁፍ ይሆናል፣ በራስጌ ላይ ቋንቋው ይጠቀሳል።



9 ኩረጃ በጥብቅ የተከለከለ ነው፣ እጅግ ተመሳሳይና አጠራጣሪ የሆኑ መልሶች አንቀበልም።

10 የሽልማት መቀበያ ቀጠሮ እስከ ሶፈር ወር መጨረሽ 1437 ዓ\ህ ይሆናል።

11 የተወዳዳሪው\ሪዋ እድሜ ከ10 ዐመት ያላነሳ መሆን አለበት።

## የውድድሩ አሸናፊዎች ሽልማት

1ኛ ደረጃ 1500 ሪያል።

2ኛ ደረጃ 1250 ሪያል።

3ኛ ደረጃ 1000 ሪያል።

4ኛ በሚቀጥሉት እርከን ያሉ ተሸላሚዎች እንደየ ቋንቋዎቹ ተሳታፊዎች ብዛት ይወሰናል።

ለተጨማሪ ማብራሪያ በ 00966505697461 ይደውሉ፥

ሼኽ ጀማል ሼኽ ሙሀመድ አህመድ

በረብዋ የደዕዋህ መከተብ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ትርጉምና ደዕዋህ ክፍል ሀላፊ



## የረብዋህ የደዕዋህ ቢሮ የወርሀ ሮመዳን የውድድር ጥያቄዎች 1436 ዓ/ሀ

### ትክክለኛ መልስ ምረጥ

1 የዚህ የ እምነት መሰረቶች ትንታኔ መጽሃፍ ደራሲ ማነው?

1 ሼኽ ኢብኑ ባዝ
2 ሼኽ ኢብኑ ዑሴይሚን
3 ሼኽ አልባኒ
4 ሼኽ ኢብኑ ቴይሚያህ

2 የእስላም መዕዘናት በ__________ አማካይነት በተላለፈው ነብያዊ ሀዲስ ውስጥ የተመለከቱት 5 መዕዘናት ናቸው።

1 ኢብኑ ዑመር
2 አቡ ሁሬይራ
3 አነስ
4 ኢብኑ ዐባስ

3 በአላህ ሱ/ወ ማመን ___________ ያጠቃልላል።

1 የአላህ መኖርን ማመን
2 የአላህ ጌትነትን ማመን
3 በአምላክነቱ በስሞቹና በባህሪያቱ ማመን
4 ሁሉም መልስ ናቸው

4 __________ የአላህ መኖርን ያመለክታሉ።

1 የተፈጥሮ አስረጅነት
2 የአእምሮ አስረጅነት
3 የሸሪኣና ህዋሳዊ ግንዛቤ አስረጅነት
4 ሁሉም መልስ ናቸው

5 አላህ ሱ/ወ ለነቢዩ _______ በብትራቸው በህሩን እንድመቱ አዟቸው መተውት ባህሩ 12 ቦታ ተከፍሎ ደረቅ መሻገሪያ መንገዶች ሆኖላቸው ነበር።

1 ኢብራሂም ዐ/ሰ
2 ሙሳ ዐ/ሰ
3 ኑህ ዐ/ሰ
4 ሙሐመድ ሰ/ዐ/ወ

6 አላህ ሱ/ወ ከብርሃን ፈጥሮአቸው ለትእዛዞቹ በፍጹምነት የመመራትና የመተግበር ሀይል የሰጣቸው ፍጡራን አሉ። እነዚህ ፍጡራን ማን ናቸው?

1 ነቢያት
2 መላእክት
3 ጅንዎች
4 መልሱ የለም



7 በዚህ መጽሃፍ ውስጥ እንደተጠቀሰው አላህ ባወረዳቸው መጻህፍት ማመን ስንት ጉዳዮችን ያካትታል?

1 3

2 4

3 7

4 መልሱ የለም

8 ከቁርኣን በፊት የነበሩት መለኮታዊ መጻህፍት በሙሉ በቁርኣን ተሽሯል፡ ይህንኑ በማስመልከት አላህ ሱ/ወ እንዲህ ብሏል። " ወዳ አንተም መጽሃፉን ከበፊቱ ያለውን መጽሃፍ አረጋጋጭና በሱ ላይ ተጠባባቂ ሲሆን በውነት አወረድን" ይህ አያ የምገኘው የት ነው?

1 ሱረቱ አል በቀረህ አያት 48

2 ሱረቱ አልማእዳህ አያት 48

3 ሱረቱ አልማእዳህ አያት 56

4 ሱረቱ አልአንፋል አያት 34

9 ነቢዩ ሙሀመድ ሰ/ዐ/ወ የነብያት መደምደሚያ መሆናቸውን አላህ ሱ/ወ የገለጸው በየትኛው የቁርኣን ሱራ ውስጥ ነው?

1 ሱረቱ አል ፋትሃ

2 ሱረቱ አልተውባህ

3 ሱረቱ አልአህዛብ

4 ሱረቱ ሙሀመድ ሰ/ዐ/ወ

10 በመጨረሻው ቀን ማመን ________ያጠቃልላል።

1 ከሞቱ በኋላ ዳግም መቀስቀስ መኖሩን ማመን

2 ምርመራ መኖሩንና ለሁሉም እንደየሥራው ዋጋ የሚሰጠው መሆኑን ማመን

3 ገነትና እሳት (ገሀነም) መኖሩን ማመን

4 ሁሉም መልስ ነው

11 በዚህ መጽሃፍ ውስጥ በቀደር ማመን በምያጠቃልላቸው ነጥቦች ስር በ2ኛነት የተጠቀሰው የቱ ነው?

1 አላህ ነገሮችን ሁሉ የሚያውቅ መሆኑን

2 አላህ ነገሮችን ሁሉ በተጠበቀው ሰሌዳ ላይ የጻፈው መሆኑን

3 ክስተቶች ሁሉ በአላህ ሱ/ወ ፈቃድና በርሱ ማሸት ብቻ የሚፈጸሙ መሆናቸውን

4 ሁሉም መልስ ነው

አላህ ሱ/ወ መልካም እድል ይወፍቃችሁ!



المسابقة الثقافية
الرمضانية السابعة عشر
للجاليات ١٤٣٦هـ






ننشر الإسلام بـ ١٠٠ لغة

በ 100 ቋንቋዎች እስልምናን እናሰራጫለን።

# Islamhouse.com


المكتب التعاوني للدعوة وتوعية الجاليات بالربوة

هاتف: ٩٦٦١١٤٤٥٤٩٠٠+ فاكس: ٩٦٦١١٤٩٧٠١٢٦+

ص ب: ٢٩٤٦٥ الرياض: ١١٤٥٧

ISLAMIC PROPAGATION OFFICE IN RABWAH

P.O.BOX 29465 RIYADH 11457 TEL: +966 11 4454900 FAX: +966 11 4970126

OFFICERABWAH